http://ethcriminalawnetwork.com

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ

ፍትሕ ሚኒስቴር

የካቲት 25/2003 ዓ.ም

http://ethcriminalawnetwork.com

# ማውጫ

**መግቢያ** ........ I

**ክፍል አንድ፡- የፖሊሲው መሠረታዊ ዓላማዎች፣ ግቦች፣ መርሆዎችና ስትራቴጂዎች** ........ 1

1.1 ጠቅላላ ........ 1

1.2 የፖሊሲ ዓላማዎች ........ 1

1.3 የፖሊሲ ግቦች ........ 2

1.4 ፖሊሲው የሚመሠረትባቸው መርሆዎች እና ስትራተጂዎች ........ 2

1.5 የስትራቴጅያዊ እና የማሻሻያ እርምጃ የሚወሰድባቸው ዘርፎች ........ 4

1.6 የፖሊሲው ተፈፃሚነት ወሰን እና የማስፈፀም ኃላፊነት ........ 4

**ክፍል ሁለት፡- ወንጀል መከላከል** ........ 5

2.1 ጠቅላላ ........ 5

2.2 ወንጀልን በመከላከል ረገድ የፍትሕ ሚኒስቴር ሚና ........ 6

2.3 ወንጀልን በመከላከል ረገድ የፖሊስ እና የደህንነት ተቋማት ሚና ........ 6

2.4 በወንጀል መከላከል ረገድ ሌሎች አካላትን የማቀናጀት ኃላፊነት ........ 7

2.5 ወንጀል እና በወንጀል ተጐጂነትን መቆጣጠርና መገምገም ........ 7

2.6 የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት የመረጃ አያያዝ ........ 7

**ክፍል ሦስት፡- የወንጀል ምርመራ እና የዓቃቤ ሕግ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደትን ስለማሻሻል** ........ 8

3.1 የወንጀል ሕግን ማስፈፀም ........ 8

3.2 የሕዝብ ተሳትፎን ስለማጐልበት ........ 8

3.3 የመርማሪዎች እና የዓቃቤያነ-ሕግን አቅም ማጐልበት ........ 9

3.4 የወንጀል ምርመራ ዓላማ እና መርሆ ........ 9

3.5 የወንጀል መርማሪዎች እና የዓቃቤያነ ሕግ ሚና ........ 10

3.6 ውጤታማ እና ቀልጠፋ የምርመራ ሥርዓትን መፍጠር ........ 11

3.7 የምርመራ ሥራ የሚጠናቀቅበትና ክስ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብ ........ 11

3.8 በወንጀል ምርመራ እና በዓቃቤ-ሕግ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ ተግባራዊ የሚደረጉ የቁጥጥር ዘዴዎች ........ 12

3.9 የወንጀል ምርመራ የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች ........ 12

3.10 በምርመራ መዛግብት ላይ የሚሰጡ ውሣኔዎች ........ 13

3.11 በወንጀል ጉዳይ ላይ ክስ ላለማቅረብ የሚሰጡ ውሣኔዎች ........ 14

3.12 ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ክስ የማይመሠረትባቸው ጉዳዮች ........ 14

http://ethcriminalawnetwork.com

3.13 ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ክስ የሚመሠረትባቸው የወንጀል ጉዳዮች ..... 16

3.14 ቅድሚያ ስለሚሰጣቸው የወንጀል ጉዳዮች ..... 16

3.15 ስለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ልዩ ክትትልና ሥልጣን ..... 16

3.16 የማስረጃ ሕጋዊነት እና ማስረጃን ማሰባሰብ፣ ማኖርና በጥቅም ላይ ማዋል ..... 17

3.16.1 ስለማስረጃ ሕጋዊነት ..... 17

3.16.2 ተጠርጣሪን ስለመያዝ፣ ስለማሰርና ብርበራ ስለማካሔድ ..... 17

3.16.3 የወንጀል ፍሬን ስለማዕግድ እና ስለመውረስ ..... 19

3.17 ልዩ የምርመራ ዘዴዎች አስፈላጊነት ..... 19

3.17.1 ሠርጐ መግባትና ክትትል ስለማድረግ ..... 20

3.17.2 የግል መገናኛ ዘዴዎችን መጥለፍ ..... 21

3.17.3 ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የግል መገናኛ ዘዴዎች የሚጠለፉባቸው ሁኔታዎች ..... 21

3.17.4 የወንጀል መረጃን ለሚያቀብሉ ሰዎች እና ወኪሎች የሚደረግ ጥበቃ ..... 22

3.17.5 በወንጀል ተካፋይ የነበረን ተጠርጣሪ ከክስ ነፃ ስለማድረግ ..... 22

3.18 ስለቀዳሚ ምርመራ ..... 23

3.19 የምስክሮች ጥበቃ ..... 24

3.20 ስለኤግዚቢት አያያዝና አስተዳደር ሥርዓት ..... 25

3.21 የዋስትና ጉዳዮች ..... 27

3.21.1 የዋስትና ጥያቄን ለመቀበል ሊተኮርባቸው የሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ..... 27

3.21.2 በቅድመ ሁኔታዎች በዋስ ስለመለቀቅ ..... 27

3.21.3 በሕግ ዋስትና የማያሰጡ የወንጀል ዓይነቶች ..... 28

3.22 ዓለም አቀፍ ትብብር ..... 28

3.22.1 ጠቅላላ ..... 28

3.22.2 የዓለም አቀፍ ትብብር ዓይነቶችና አፈፃፀማቸው ..... 28

**ክፍል አራት፡- የወንጀል ፍትሕ ሂደቱን ውጤታማነትና ፍትሐዊነት ስለማሻሻል ..... 29**

4.1 ጠቅላላ ..... 29

4.2 የወንጀል ጉዳዮችን አያያዝ ዘመናዊ ስለማድረግ ..... 30

4.2.1 ጠቅላላ ..... 30

4.2.2 የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን ..... 31

4.3 የተቀላጠፈ እና የተፋጠነ የፍርድ አሰጣጥ ሂደት ስለሚመራበት ሥነ-ሥርዓት ..... 31

4.3.1 ጠቅላላ ..... 31

4.3.2 ተከሳሽ ወይም ምስክር ፍርድ ቤት ስለማቅረብ ..... 32

4.3.3 ቀልጣፋ የወንጀል ክርክር ስለሚመራበት ሥነ-ሥርዓት ..... 32

4.3.4 በተፋጠነ የወንጀል ፍትሕ አሰጣጥ ሂደት የሚታዩ የወንጀል ጉዳዮች አያያዝ ..... 32

http://ethcriminalawnetwork.com

4.3.4.1 መርህ ..... 32
4.3.4.2 የተፋጠነ የወንጀል ፍትሕ አሰጣጥ ሂደት የሚመራበት ሥነ-ሥርዓት..... 33
4.4 የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሽ ስለሚዛወርበት ሁኔታ..... 33
4.5 ማስረጃን ስለመግለፅ፣ ጥፋተኝነትን ስለማመን እና የጥፋተኝነት ድርድር..... 33
4.5.1 ጠቅላላ ..... 33
4.5.2 ማስረጃ ስለማስታወቅ ወይም ስለመግለጽ ..... 34
4.5.3 ማስረጃን ማስታወቅ ወይም መግለጽ ቀሪ ስለሚሆኑባቸው ልዩ ሁኔታዎች..... 35
4.5.4 የጥፋተኝነት ድርድር እና ጥፋተኝነትን ስለማመን..... 36
4.5.4.1 የጥፋተኝነት ድርድር ዓላማና አካሔድ ..... 36
4.5.4.2 የጥፋተኝነት ድርድር አሠራርን ለመዘርጋት ሕጎችን ስለማሻሻል..... 36
4.5.4.3 ጥፋተኝነትን ስለማመን..... 37
4.5.5 ክስን ስለማንሣት ወይም ክርክርን ስለማቋረጥ ..... 37
4.6 ከመደበኛ የፍርድ ሂደት ውጭ ያሉ አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች..... 38
4.6.1 ጠቅላላ ..... 38
4.6.2 አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች..... 38
4.6.2.1 መርህ ..... 38
4.6.2.2 የአማራጭ መፍትሔ እርምጃ መስፈርቶች..... 39
4.6.2.3 አማራጭ የመፍትሔ እርምጃ ተፈፃሚ ስለሚሆንበት ሁኔታዎች..... 39
4.6.2.4 ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ስለሚዘረጋው ሥርዓት ..... 40
4.6.2.5 በዓቃቤ ሕግ ስለሚወሰን አማራጭ የመፍትሔ እርምጃ ..... 40
4.7 በጠበቃ ስለመወከልና የተከላካይ ጠበቆችን ሙያዊ ብቃትና ሥነ-ምግባር ስለማጎልበት..... 41
4.7.1 በጠበቃ ስለመወከል..... 41
4.7.2 የተከላካይ ጠበቆች ሙያን ስለማጎልበት..... 42
4.8 የይግባኝ ሥርዓትን ስለማጠናከርና የካሣ ክፍያ..... 42
4.8.1 የይግባኝ ሥርዓትን ስለማጠናከር ..... 42
4.8.1.1 ስለይግባኝ ..... 43
4.8.1.2 ስለሰበር..... 43
4.8.1.3 የመጨረሻ ውሣኔን እንደገና ስለማየት..... 43
4.8.2 የካሣ ክፍያ ..... 43
4.9 የኮምፒውተርና የኢንተርኔት ወንጀሎች ..... 44
4.10 የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱን አፈፃፀም ስለመከታተል..... 45
4.11 በፌዴራልና በክልል የፍትሕ አካላት መካከል ስለሚኖር የሥራ ትብብር እና ግንኙነት..... 45

http://ethcriminalawnetwork.com

**ክፍል አምስት፡- የወንጀል ቅጣት አፈፃፀም ፍትሐዊነትና ውጤታማነትን ስለማሻሻል** ............ **46**

5.1 የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ይዘት ............ 46

5.2 የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ስለማዘጋጀት ............ 47

5.3 ቅጣትንና ሌሎች እርምጃዎችን ስለማስፈፀም ............ 47

**ክፍል ስድስት፡- በጋራ መብቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን የወንጀል ድርጊት ስለማድረግ እና ጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ስለሚደረግ የተለየ አያያዝ** ............ 48

6.1 በጋራ መብቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ወይም ጉዳቶችን የወንጀል ድርጊት ስለማድረግ ............ 48

6.2 በወንጀል ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች መብት ስለማስከበር ............ 49

6.2.1 የተጐጂዎች በወንጀል ምርመራ፣ ክስ እና የፍርድ ሂደት ተሳትፎ የማድረግና መረጃ የማግኘት መብት ............ 50

6.3 የሕፃናት ወይም የወጣቶች የወንጀል ፍትሕ መሠረታዊ መርሆች ............ 51

6.4 የወጣት ወንጀል አድራጊዎች አያያዝ ............ 51

6.4.1 ጠቅላላ ............ 51

6.4.2 ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች የሚደረግ የሕግ ከለላ ............ 52

6.4.3 የአማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች ተመራጭነት ............ 52

6.4.4 የአማራጭ የመፍትሔ እርምጃች አፈፃፀም ............ 52

6.4.5 ስለልዩ ክፍሎች መቋቋም ............ 52

6.5 ለወንጀል ተጋላጭ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ትኩረት ስለመስጠት ............ 53

**ክፍል ሰባት፡- ልዩ ልዩ ጉዳዮችና አቅጣጫዎች** ............ **53**

7.1 መሻሻል ወይም መለወጥ ስለሚገባቸው ጉዳዮች ............ 53

7.2 የፖሊሲው የተፈፃሚነት ጊዜ ............ 54

# መግቢያ

ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ፖሊሲ አቅጣጫዎች መካከል የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን፣ የግለሰቦችንና የሀገርን ሠላምና ደህንነት ማስጠበቅ ቀዳሚ አጀንዳ መሆኑ ይታወቃል። የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን፣ የግለሰቦችንና የሃገርን ሰላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ በማረጋገጥ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እና መልካም አስተዳደር ለመገንባት እንዲሁም ልማትና ዕድገትን ለማፋጠን እየተደረጉ ያሉትን ጥረቶች በይበልጥ አጠናክሮ ማስቀጠል የግድ ይላል። እነዚህን ጥረቶች በይበልጥ አጠናክሮ ለማስቀጠል የሚረዱ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ደግሞ በሕግ የበላይነት ላይ የተመሠረተ ፍትሐዊ፣ ሚዛናዊ፣ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ተገማች እና ወጥ የሆነ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው ውጤታማ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት መኖር ያስፈልጋል።

በሀገሪቱ ለዘመናት ተንሰራፍተው ከነበሩ ፀረ-ዲሞክራሲያዊ አገዛዞች የተወረሱና በየጊዜው በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠሩ ችግሮች የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱን ውስን አቅም ክፉኛ እየተፈታተኑት ይገኛሉ። ለእነዚህ ችግሮች መፈጠር በሀገራችን ወንጀልን ለመከላከል የሚደረገው እንቅስቃሴ በጥናት ላይ የተመሠረተና በቂ ትኩረት የተሰጠው አለመሆን፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተወሳሰቡና ዓለም አቀፍ ገፅታ ያላቸውና ከባድ ጉዳት የሚያደርሱ እንደ ሽብርተኝነት፣ በተደራጁ ቡድኖች የሚፈፀሙ ወንጀሎች፣ የኢኮኖሚ እና የሙስና ወንጀሎች በዓይነታቸው፣ በብዛታቸው እና በአፈፃፀም ሥልቶቻቸው መበራከት በመንስዔነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን ከሕገ መንግሥቱ ጋር ለማጣጣም ብዙ ሥራዎች የተሠሩ ቢሆንም ከወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሲታዩ ግልጽነት የሚጎድላቸው፣ ኋላቀርና መሠረታዊ ክፍተት ያሉባቸው፣ የፍትሕ አካላት ለኅብረተሰቡ እና ለመንግሥት የሚሰጡት አገልግሎት በግልጽነት፣ በተጠያቂነትና በፍትሐዊነት መርሆች ላይ የተመሠረቱ አለመሆን፣ ሂደቶቹም ረጅም ጊዜ የሚወስዱና የተንዛዙ፣ ኋላቀርና ከፍተኛ ወጭ የሚያስከትሉ እንዲሁም ከቢሮክራሲያዊ አደረጃጀትና አሠራር ዘይቤ ያልተላቀቁ መሆናቸው ለችግሮቹ መፈጠር በተጨማሪ እንደመንስዔነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። በፍትሕ አካላት መካከል ሊኖር የሚገባው ሀገራዊ ራዕይ ላይ የተመረኮዘ የሥራ ትብብርና ግንኙነት በሚፈለገው ደረጃ ያለመኖር እና በመስኩ የተሠማሩ ባለሙያዎች የአመለካከት፣ የሥነ-ምግባርና ሙያዊ ብቃት ደረጃ አነስተኛ መሆን እና የመሳሰሉ ጉድለቶች በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ለተፈጠሩ ችግሮች በመንስዔነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

http://ethcriminalawnetwork.com

ከላይ በተጠቀሱትና ተያያዥነት ባላቸው ምክንያቶች ፍትሕ ሥርዓቱ ቀልጣፋ፣ ፍትሐዊ፣ ተደራሽ፣ በግልጽነትና ተጠያቂነት ላይ የተመሠረተና ውጤታማ የሆነ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ ለማቅረብ ካለመቻሉ የተነሳ ሕዝቡ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደሩ ሂደት ውስጥ ያለውን ተሳትፎና በሥርዓቱ ላይ ያለውን አመኔታ የሚሸረሽሩ ሁኔታዎች እያጋጠሙ ይገኛሉ፡፡ አሁን እየታዩ ያሉ ችግሮች በአፋጣኝና ሥርዓት ባለው መልኩ ካልተፈቱ በየጊዜው ሊፈጠሩ ከሚችሉ ተጨማሪ ችግሮች ጋር ተዳምሮ ተስፋ ሰጭ በሆነ ሁኔታ እየተፈፀመና ውጤታማ እየሆነ ያለውን የዕድገትና የልማት ዕቅዳችንን ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲሁም የዳበረ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት፣ መልካም አስተዳደር እና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን በምናደርገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ መፍጠራቸው አይቀሬ ነው፡፡ በመሆኑም የተጠቀሱትን ችግሮች ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ለመፍታት ወይም ለማቃለል በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች በሚሸፍን አኳኋን የተጠናከሩና ዘላቂነት ያላቸው በፖሊሲ ላይ የተመሠረቱ ርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

ፖሊሲው በአንድ በኩል ለወንጀል መነሻ የሚሆኑ ምክንያቶችን በመቀነስ ወይም በማጥፋት፣ በሌላ በኩል የተፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮች በመደበኛ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር እና ከዚያ ውጭ ባሉ ሌሎች አማራጭ መንገዶች ተገቢና ዘላቂ መፍትሔ የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት ጊዜው የሚጠይቀውንና ደረጃውን የጠበቀ የኅብረተሰቡን ፍላጎት የሚያረካ በግልጽነትና ተጠያቂነት መርሆች ላይ የተመሠረተና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ፍትሕ ሥርዓት ለመገንባት ያስችላል፡፡ ይህም ለወንጀል ፍትሕ አስተዳደር የሚመደበውን የሕዝብ ኃብት ጠቃሚና ውጤት በሚያስገኝ ሥራ ላይ እንዲውል ይረዳል፡፡ ስለዚህ ይህ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ የተጠቀሱትን አሠራሮች ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ በዋናነት በሕገ መንግሥቱ ቀጥሎም በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ የሰፈሩትን መርሆችና ድንጋጌዎችን እንዲሁም አለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያላቸው የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት የአሠራር ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ ተቀርጿል፡፡

ፖሊሲው ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ የቀረበ ሲሆን በይዘቱም ዋና ዋና የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ጉዳዮችን የሚሸፍን ነው፡፡ በመሆኑም ከወንጀል መከላከል ጀምሮ የወንጀል ምርመራና ክስ፣ ፈጣንና ፍትሐዊ የፍርድ ሂደት፣ በገለልተኛ ፍርድ ቤት የመዳኘትን እና በፍርድ ቤት የተወሰነን ቅጣት ማስፈፀምን ጨምሮ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር የሚሰጡ የውሳኔ ሂደቶችን ያጠቃልላል፡፡

ፖሊሲውን በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል እንዲቻል የሕዝቡን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ድጋፍ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም ለሚጠበቀው ውጤት የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ተቋማት የሆኑት የመርማሪ አካላት፣ የዐቃቤ ሕግ፣ የተከላካይ ጠበቆች፣ የፍርድ ቤቶች፣ የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር እና የሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የተሟላ ቅንጅታዊ አሠራርና ድጋፍ ያስፈልጋል፡፡

ፖሊሲው ያስቀመጣቸው አቅጣጫዎች ኅብረተሰቡ በየጊዜው የሚያስመዘግባቸውንና በሰው ኃይል፣ በፋይናንስ እና በተቋማት ረገድ ወደፊት የሚፈጠሩ ለውጦችን ሊያስተናግድ በሚችል መልኩ ሁሉን አቀፍ ሆኖ የቀረበ ነው፡፡ እንዲሁም የፍትሕ ሚኒስቴርን እና የሌሎች የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ አካላት የሆኑ የመርማሪ አካላትን፣ የዐቃቤ ሕግን፣ የተከላካይ ጠበቆችን፣ የፍርድ ቤቶችን እና የማረሚያ ቤቶችን አቅም መገንባት አስፈላጊነት ላይ አፅንኦት ይሰጣል፡፡ በዚህም በአጠቃላይ በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ጠንካራ የሆነ የአመራር አቅም መገንባት የሚገባው መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሌላም በኩል ፖሊሲው ተዛማጅ የሆኑና በሥራ ላይ ያሉ እንደ ወንጀል እና የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ያሉ ሕጐችን ለማሻሻል ወይም ወደፊት አዳዲስ ሕጐችን ለማውጣት እንዲሁም ሌሎች የአሠራር ሥርዓቶች ለማዘጋጀት እንደመነሻና መሠረታዊ አቅጣጫ ጠቋሚ መሣሪያ ያገለግላል፡፡

ፖሊሲው በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ያሉ ሁሉም አካላት የሚጠበቅባቸውን የሥራ ድርሻ እና የተጣሉባቸውን ግዴታዎች ሚዛናዊ፣ ኃላፊነትን በተላበሰ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት አኳኋን ማከናወን እንዳለባቸው የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በተጨማሪም በዚህ መስክ ተሰማርተው በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ባለሙያዎችና ሠራተኞች በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ለሚያከናውኑት ለማንኛውም ተግባር በተናጠልም ሆነ በጋራ ለሀገሪቱ ሕዝብና መንግሥት ተጠያቂነት ያለባቸው መሆኑን ፖሊሲው ያስረዳል፡፡ እነዚህ ባለሙያዎችና ሠራተኞች የሀገሪቱ የወንጀል ሕጎች እና ሙያው በሚጠይቀው ደረጃና ብቃት እንዲሁም የሙያው የሥነ ምግባር መርሆዎችና ደንቦች ላይ በመመሥረት የመፈፀምና የማስፈፀም ግዴታ አንዳለባቸው ከፖሊሲው መረዳት ይቻላል፡፡

ፖሊሲው ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የአፈፃፀሙን ሂደት የሚያቀላጥፉ የተለያዩ የአሠራር መመሪያዎች እና የተለያዩ አካላት ለትግበራ የሚጠቀሙባቸው ዝርዝር የማስፈፀሚያ ሠነዶች ሊዘጋጁ እንደሚገባ ታሣቢ ተደርጓል፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ ለሁሉም የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ባለሙያዎች ውጤታማ የሆነ የሥልጠና ኘሮግራም በመቅረጽ ተግባርና ኃላፊነታቸውን በተሻለ የውጤታማነት እና የብቃት ደረጃ ማከናወን የሚያስችላቸውን ዕውቀትና ክህሎት ማስጨበጥ አስፈላጊ መሆኑ በፖሊሲው ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በሀገራችን ያለውን የወንጀል ሁኔታ ለመከታተልና የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱን የተለያዩ ተቋማትና አካላት የክንዋኔ እና የአፈፃፀም ደረጃ በቅርበት ለመከታተልና ለመገምገም እንዲሁም የሥራ አፈፃፀማቸውን ለማሻሻል የሚያስችል መረጃ ለማግኘት ውጤታማ የወንጀል መረጃ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

ፖሊሲው ሰባት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል የፖሊሲው መሠረታዊ ዓላማዎችን፣ ግቦችን፣ መርሆዎችንና ስትራቴጂዎችን እንዲሁም የተፈፃሚነት ወሰን፤ ሁለተኛው ክፍል ወንጀል መከላከልን፤ ሦስተኛው ክፍል የወንጀል ምርመራ እና የዐቃቤ ሕግ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ማሻሻልን፤ ክፍል አራት የወንጀል ፍትሕ ሂደት ውጤታማነትና ፍትሐዊነት ማሻሻልን፤ ክፍል አምስት የወንጀል ቅጣቶች የአስተዳደርና የአፈፃፀም ውጤታማነት ማሻሻልንና ማሳደግን፤ ክፍል ስድስት አሁን ያለው የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ለወንጀል ድርጊት ተጎጅዎች፣ ለወንጀል ተጋላጭ ለሆኑ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች እና ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች የሚያደርገውን የአያያዝ እና የሚስተናገድበትን አሠራር የተሻለ ማድረግን እንዲሁም በጋራ መብቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ወንጀል ስለማድረግ፤ የፖሊሲው የመጨረሻ ክፍል ልዩ ልዩ ጉዳዮችንና አቅጣጫዎችን ይመለከታል፡፡

በመጨረሻም የፖሊሲው መፅደቅና ወደ አፈፃፀም መሸጋገር ለሀገሪቱ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት በርካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመጀመሪያ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተካተቱና ለወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ አግባብነት ያላቸው መርሆች፣ ድንጋጌዎችና ዕሴቶች ከሁሉም በተሻለ መልኩ እንዲተገበሩ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡ ሁለተኛ በወንጀል ፍትሕ ዘርፍ የተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍ ከለመኖሩ የተነሣ ለዘመናት በሥርዓቱ ውስጥ ተፈጥረው የነበሩ ችግሮችን የበለጠ ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ ዓይነተኛ መሣሪያ ይሆናል፡፡ በመጨረሻም ፖሊሲው ለወንጀል ፍትሕ ሥርዓታችን አዳዲስ የሆኑ በርካታ የሕግ አስተሳሰቦችን፣ አሠራሮችንና ሥነ-ሥርዓቶችን የሚያስተዋውቅ እንደመሆኑ በሀገሪቱ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ እንደ አንዱ መሠረታዊ የለውጥ ኩነት ሊቆጠር ይችላል፡፡ በአጠቃላይ ይህ ፖሊሲ የሀገሪቱን የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ለሕዝቦቿ፣ ለማኅበረሰቧ፣ ለዜጎቿና ለነዋሪዎቿ ምቹ ለማድረግ የሚከናወኑ ሥራዎችን ግልጽና በታወቀ የአሠራር፣ የአመራርና የአደረጃጀት ሥርዓት ለማከናወንና ውጤታማ ለማድረግ በእጅጉ ይረዳል ተብሎ ይታመናል፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com

# ክፍል አንድ

## የፖሊሲው መሠረታዊ ዓላማዎች፣ ግቦች፣ መርሆዎችና ስትራቴጂዎች

### 1.1 ጠቅላላ

ይህ ፖሊሲ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ውስጥ የተካተቱትን ወይም በሕገ-መንግሥቱ መሠረት ዕውቅና ያገኙትን እና ለወንጀል ፍትሕ ሥርዓት አግባብነት ያላቸውን መሠረታዊ መርሆዎች፣ ድንጋጌዎች እና ዕሴቶች አካቶ የያዘ ነው፡፡ በተጨማሪም ፖሊሲው እነዚህን ሕገ-መንግሥታዊ መርሆዎች፣ ድንጋጌዎችና ዕሴቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚሠሩ ሥራዎችና የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች መሠረት የሚያደርጓቸውንና የሚመሩባቸውን መሠረታዊ የመንግሥት ውሣኔዎችንና አቅጣጫዎችን የሚያሳይ ነው፡፡

### 1.2 የፖሊሲ ዓላማዎች

ይህ ፖሊሲ የሚከተሉት አራት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት፡፡ እነዚህም፡-

1. የኢትዮጵያ ብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችን፣ ሕዝቦችን፣ መንግሥትንና ግለሰቦችን ከወንጀል ጥቃት በመከላከል ሰላምና ደህንነታቸውን ማረጋገጥ፤
2. በሕገ-መንግሥቱና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ የሚሰነዘሩ የወንጀል ድርጊቶችን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትና የሥርዓቱን ዘላቂነት ማረጋገጥ፤
3. መልካም አስተዳደር፣ ዴሞክራሲና ሰላም የሰፈነባት እንዲሁም የለማች ሀገር ለመገንባት እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች እንዲጠናከሩ እና ቀጣይነት እንዲኖራቸው የበኩሉን ድርሻ ማበርከት፤ እና
4. ከወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ጋር በተያያዘ የግለሰቦችን መብትና ነፃነት ለማስከበር የሚያስችል የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት መገንባት ወይም መዘርጋት፤

ናቸው፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com

## 1.3 የፖሊሲ ግቦች

ይህ ፖሊሲ የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች አሉት፡፡ እነሱም፡-

(ሀ) የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱን የውጤታማነት፣ የፍትሐዊነት፣ የሚዛናዊነት፣ የተደራሽነት፣ የቅልጥፍና፣ የተገማችነትና የወጥነት የግልጽነትና የተጠያቂነት ደረጃ እምርታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ማስቻል፤

(ለ) ለሕገ መንግሥቱ ታማኝ የሆኑ፣ ሙያዊ ብቃት፣ መልካም አመለካከትና ሥነ ምግባር ያላቸው እና ደረጃቸውን የጠበቁ ሙያተኞችንና የወንጀል ፍትሕ ተቋማትን በመፍጠርና በመገንባት ኅብረተሰቡ በሚቀርብለት የሕግና የፍትሕ አገልግሎት ላይ ያለውን አመኔታና ከአገልግሎቱ የሚያገኘውን እርካታ መሠረታዊ ለውጥ በሚያመጣ መልኩ ማሳደግ፤

(ሐ) በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ አስተዋፅኦ ባላቸው የተለያዩ ተቋማት እና አካላት መካከል ሊኖር የሚገባውን ትብብር እና ቅንጅታዊ አሠራር መፍጠርና ማጎልበት፤

(መ) በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ሰፊ የሆነ የሕዝብ ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ማስቻል፤

(ሠ) ከወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ የሚጠበቁ ውጤቶችን ለማስመዝገብ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትንና ፕሮግራሞችን መፍጠርና መርሀ ግብሮችን ማዘጋጀት፤

(ረ) በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ አዲስ ለሚወጡ ወይም ማሻሻያ ለሚደረግባቸው ሕጎች መሠረት የሚሆን አቅጣጫ ማስቀመጥ፤ እና የመሳሰሉ ናቸው፡፡

## 1.4 ፖሊሲው የሚመሠረትባቸው መርሆዎች እና ስትራተጂዎች

ይህ ፖሊሲ በሚከተሉት መርሆዎች እና ስትራተጂዎች ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተካተቱትን እና ለወንጀል ፍትሕ ሥርዓት አግባብነት ያላቸውን መርሆዎች፣ ድንጋጌዎች እና ዕሴቶች ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ይፈፀማሉ፤

(ለ) በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት በሕገ መንግሥቱ መሠረት የኢትዮጵያ የሕግ አካል በሆኑ ከዓለም አቀፍ ሕጎች፣ ስምምነቶችና ሠነዶች እንዲሁም ከዓለም አቀፍ የትብብር ዓላማዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ ይፈፀማሉ፤

(ሐ) በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት የሚሰጡ አገልግሎቶች ውጤታማ፣ ፍትሐዊ፣ ሚዛናዊ፣ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ተገማች፣ ወጥነት፣ ግልፅነት፣ ተጠያቂነት እና ከፍተኛ የሕዝብ አመኔታ ባለው አሠራር ለተገልጋዩ ኅብረተሰብ ይቀርባሉ፤

(መ) የወንጀል መከላከል ስትራቴጂዎች በዋናነት የወንጀልና የወንጀል ስጋት መንስዔዎችን ለመረዳት በሚደረጉ የጥናት ውጤቶች እንዲሁም ወንጀልን በመከላከል እና የሚፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶችን በመቀነስ ረገድ ውጤታማ የሆኑ አሠራሮችን እና መልካም ተሞክሮዎችን መሠረት በማድረግ ይነደፋሉ፤

(ሠ) የወንጀል ፍሬ የሆኑ ንብረቶችንና ገንዘቦችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመያዝ፣ ለማገድ፣ ለመውረስ ወይም ለማስተዳደር የሚያስችል ግልጽና ዝርዝር የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይሆናል፤

(ረ) በወንጀል ጉዳይ ላይ ውሣኔ የሚሰጥበት ሂደት ንፁኃን ከአጥፊዎች በአግባቡ የሚለዩበት፣ ጥፋተኛ ሆነው የተገኙት ከፈፀሙት ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ ቅጣት የሚያገኙበት፣ ለጥፋታቸው ኃላፊነት መውሰዳቸው የሚረጋገጥበት እና በወንጀሉ የተፈጠሩ ችግሮችን በማስወገድ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ ይሆናል፤

(ሰ) በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ የሚሰጡ ማናቸውም ውሣኔዎች ወንጀል ለመከላከል፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የሁሉንም ሰዎች መብት ለማስከበር እና የሀገርንና የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ይሆናሉ፤

(ሸ) የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ የሕዝብ ሁለንተናዊ ተሳትፎ እንዲሁም የተለያዩ አካላት የተቀናጀ እና የተባበረ አሠራር በሚረጋገጥበት አኳኋን ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል፤

(ቀ) የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ በወንጀል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን መብት ለማስከበር እና የሚገኙበትን ልዩ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚገነባ ይሆናል፤

(በ) በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ በማንኛውም ደረጃ በሚከናወኑ ተግባራት የወጣት ወንጀል አድራጊዎች፣ የወንጀል ተጎጅ ሕፃናት፣ የወንጀል ጥፋተኛ ወይም ተጎጅ የሆኑ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና በኅብረተሰቡ ውስጥ ለወንጀል ተጋላጭ የሆኑ ሌሎች ክፍሎችን ፍላጐትና የተለዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ትኩረት ማግኘታቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ ይሆናል፡፡

## 1.5 የስትራቴጂያዊ እና የማሻሻያ እርምጃ የሚወሰድባቸው ዘርፎች

ከላይ የተመለከቱትን ዓላማዎችና ግቦች ለማሳካት በቅድሚያ የወንጀል ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ ለመከላከል፣ ተፈፅመው ከተገኙም የድርጊቱ ፈፃሚዎች ፍትሐዊ፣ ሚዛናዊ፣ ተደራሽ እና ቀልጣፋ፣ የተገማችነት፣ የወጥነት እና ከፍተኛ የሕዝብ አመኔታ ባለው አሠራር የሚቀጡበትና ከጥፋታቸው በመታረም ለወደፊቱ ከኅብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው ሰላማዊ ዜጋ ሆነው እንዲኖሩ ለማድረግ የሚያስችል የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት መገንባት አማራጭ የሌለው ተግባር ነው፡፡ የተጠቀሰውን ዓይነት የወንጀል መከላከልና የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ለመገንባት ይቻል ዘንድ ለውጥ ሊደረግባቸው እና ስልታዊ የሆኑ እርምጃዎች ሊወሰዱባቸው የሚገባቸው አምስት ዋና ዋና ጉዳዮች በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡ እነዚህም፡-

**አንደኛ፡-** ሀገር አቀፍ የወንጀል መከላከል ስትራተጂ መንደፍ እና ተግባራዊ ማድረግ፤

**ሁለተኛ፡-** የወንጀል ምርመራ እና የዐቃቤ ሕግ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደትን ማሻሻል፤

**ሦስተኛ፡-** የወንጀል ፍትሕ ሂደትን ውጤታማነትና ፍትሐዊነት ማሻሻል፤

**አራተኛ፡-** የወንጀል ቅጣቶችን የአስተዳደርና የአፈፃፀም ውጤታማነት ማሻሻልና ማሣደግ፤ እና

**አምስተኛ፡-** የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ለወንጀል ድርጊት ሰለባዎች፣ ምስክሮች፣ ለወንጀል ተጋላጭ ለሆኑ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች እና ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች የሚያደርገውን የአያያዝ ሁኔታና የሚያስተናግድበትን አሠራር የተሻለ ማድረግ፤

የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.6 የፖሊሲው ተፈፃሚነት ወሰን እና የማስፈፀም ኃላፊነት

ፖሊሲው በሁሉም  የወንጀል ጉዳዮች እና የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ተሣታፊ በሚሆኑት አካላት ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ ፍትሕ ሚኒስቴር ፖሊሲው ውጤታማ በሆነ ሥርዓት እንዲፈፀም የሚመለከታቸው አካላትን የማስተባበር፣ የማቀናጀት፣ የመምራትና የአፈፃፀም ደረጃውን ተከታትሎ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ፍትሕ ሚኒስቴር በተሻለ ሥርዓት ፖሊሲውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ማንኛውም ድጋፍንና ዕርዳታን አግባብነት ላላቸው አካላት ለማድረግ የሚያስችለውን በቂ አቅም መፍጠር ይኖርበታል፡፡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራል እና የክልል የፍትሕ አካላት እና ተቋማት

http://ethcriminalawnetwork.com

በፖሊሲው ውስጥ የተቀመጡትን አቅጣጫዎች፣ ከፖሊሲው የሚመነጩ ስትራቴጂዎችን እና ኘሮግራሞችን እንዲሁም በፖሊሲው መሠረት አዲስ በሚወጡ ወይም በሚሻሻሉ ሕጐች በተናጠልም ሆነ በጋራ የሚሰጧቸውን ኃላፊነት በአግባቡ የመወጣት ግዴታ አለባቸው፡፡

# ክፍል ሁለት

# ወንጀል መከላከል

## 2.1 ጠቅላላ

በአሁኑ ዘመን በሀገራችንም ሆነ በየትኛውም የዓለማችን ክፍል ወንጀልና የወንጀል ሥጋቶች በወልም ሆነ በግለሰብ የአኗኗር መልካም ገፅታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደሩ እና በሰብዓዊ ሀብትና ልማት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተሉ እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡

እነዚህ ማኀበራዊ ጠንቆችና ሳንካዎች ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የተረጋገጠባት፣ ሰላም የሰፈነባት እና የለማች ሀገር ለመገንባት የሚደረጉ ጥረቶች ስኬታማ እንዳይሆኑ በማድረግ ረገድ የራሳቸውን አሉታዊ ሚና እንደሚጫወቱ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም መልካም አስተዳደር፣ ዴሞክራሲ፣ ዘላቂ ሰላምና ልማት የሰፈነባት ሀገር ለመገንባት ከሚደረጉ ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች መካከል አንዱ የወንጀል መከላከል ሥርዓት መፍጠር ወሳኝ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

በመሆኑም ወንጀልን በመከላከል ሀገራችን እያደረገች ያለችውን የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጥረቶች በተጠናከረ መልኩ ለማስቀጠል ይረዳ ዘንድ በወንጀል መንስዔዎችና መከላከያ ዘዴዎች ላይ ተከታታይነት ያለው ጥናት ይከናወናል፡፡ ከጥናቱ በሚገኙ ውጤቶች እና መፍትሔዎች መሠረት ተስማሚ ስትራቴጅዎች ተነድፈው አግባብነት ያላቸው የፌዴራል እና የክልል መንግሥት አካላት በመቀናጀት እና ኅብረተሰቡንም በማሳተፍ በተግባር ላይ እንዲያውሉት ይደረጋል፡፡

በሀገር ዓቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ የወንጀል መከላከል ስትራቴጂዎች የወንጀል መስፋፋትን፣ ለወንጀል ተጋላጭነትን እና የወንጀል ሥጋት መቀነስንና በየደረጃው ያሉ የኅብረተሰቡን አደረጃጀት መሠረት ያደረጉ ይሆናሉ፡፡ የወንጀል መከላከል ተግባራት የአፈፃፀም ደረጃ ተዘጋጅተው የሚተገበሩ ስትራቴጂዎች ውጤታማነትን ለማጥናት፣ ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

## 2.2 ወንጀልን በመከላከል ረገድ የፍትሕ ሚኒስቴር ሚና

ፍትሕ ሚኒስቴር የወንጀል መከላከልን ተግባር በሀገር አቀፍ ደረጃ በመምራትና በማስተባበር ረገድ የሚከተሉት ዋና ዋና ሚናዎች ይኖሩታል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ተቋማት ጋር ለመሥራት የሚያስችል አቅምና አመቺ ሁኔታ በመፍጠር ምርጥ ተሞክሮዎችን መሠረት ያደረጉ ውጤታማ የወንጀል መከላከል ስትራቴጂዎች የሚነደፉባቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

(ለ) በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደረጉትን የወንጀል መከላከል ጥረቶች የተሣኩ ለማድረግ ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመሆን በተለያዩ የተቋማት መካከል ዘርፈ ብዙ የሆኑ የቅንጅታዊ የአሠራር ዘዴዎችን ይቀይሣል፡፡

(ሐ) በተለያየ የማኅበረሰብ ደረጃ ለሚከናወኑ የወንጀል መከላከል ሥራዎች የሚውሉ መረጃዎችን፣ የጥናትና የምርምር ዘዴዎች እና ሌሎች መገልገያዎች የሚቀርቡበትን ሁኔታዎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያመቻቻል፡፡

(መ) የወንጀል መከላከልና የወንጀል ሕግ ዓላማዎችን በተሻለ ሁኔታ ከግብ ለማድረስ እንዲያግዙ በተለያዩ አካላት የሚሠሩ የጥናትና የምርምር ውጤቶችን በማሰባሰብ እና በማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፡፡

## 2.3 ወንጀልን በመከላከል ረገድ የፖሊስ እና የደህንነት ተቋማት ሚና

የኢትዮጵያ መንግሥት የሀገርን፣ የኅብረተሰብንና የግለሰቦችን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ ወንጀልንና በወንጀል ድርጊት ተጎጅነትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እያደረጋቸው ያለው ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን ስኬታማ ከማድረግ አንፃር የሀገራችን የፖሊስና የደህንነት ተቋማት ድርሻ በጣም ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከዚህም በመነሳት የወንጀል መከላከል ተግባራት ያለእነዚህ ተቋማት ጉልህ ተሳትፎ የሚፈለገውን ውጤት ያስገኛሉ ተብሎ አይገመትም፡፡ በመሆኑም በፌዴራል እና በክልል መንግሥታት እንዲሁም የተለያዩ የኅብረተሰብ አደረጃጀቶችን መሠረት በማድረግ የሚነደፉ የወንጀል መከላከል ስትራቴጅዎችን እና ዘዴዎችን በማጥናትና በማዘጋጀት፣ በመፈፀምና በማስፈፀም፣ ውጤታቸውን በመገምገምና አግባብነት ያላቸው የማስተካከያ እርምጃዎችን በመውሰድ ሂደቶች ውስጥ በተለያዩ ደረጃ የሚገኙ የፖሊስና የደህንነት ተቋማት የማይተካ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ ይህ የማይተካ ሚናቸው በመስኩ ባሉ እና ወደፊት በሚወጡ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎች፣ ፕሮግራሞች፣ መመሪያዎችና አግባብነት ባላቸው በሌሎች የአሠራር ሥርዓቶች ውስጥ በግልጽ የተመለከተ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

### 2.4 በወንጀል መከላከል ረገድ ሌሎች አካላትን የማቀናጀት ኃላፊነት

በፌዴራል እና በክልል መንግሥታት ደረጃ የሚገኙ አግባብነት ያላቸው ተቋማት ወንጀልን የመከላከል የጋራ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን የእነዚህን ተቋማት እንቅስቃሴ ከኅብረተሰቡ፣ ከግሉ እና በመንግሥታት ስምምነት ከሚመሠረቱ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የማቀናጀቱ ኃላፊነት በፌዴራል ደረጃ የፍትሕ ሚኒስቴር ሲሆን በክልል ደረጃ ደግሞ የየክልሉ የፍትሕ ቢሮዎች ኃላፊነት ይሆናል፡፡

### 2.5 ወንጀል እና በወንጀል ተጐጂነትን መቆጣጠርና መገምገም

ወንጀልን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚቀረፁ ስትራቴጂዎችና መርሀ ግብሮች ውጤታማነት የሚለካው በሚከተሉት ዋና ዋና የክንውን ደረጃዎች ይሆናል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) ለሚመለከታቸው የፍትሕ አካላት ሪፖርት የተደረጉ የወንጀል ብዛት በተለይም በተቀረፀው ስትራቴጂ ወይም መርሀ ግብር ለመቀነስ እንደ ዓላማ በተያዙ የወንጀል ዓይነትና ብዛት፤

(ለ) በወንጀል የተጐጂነትን ደረጃ ለማወቅ በሚደረገው የዳሰሳ ጥናት፤

(ሐ) ሕዝቡ ከወንጀል ተጐጂነት መጠበቁን አስመልክቶ ያለው አስተያየት ወይም በመስኩ በሚደረገው ጥናት መሠረት የሚደረስበት የሕዝቡ የወንጀል የስጋት ደረጃ ናቸው፡፡

### 2.6 የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት የመረጃ አያያዝ

በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ በየዕለቱ የሚከናወኑ ተግባራትና የሚያጋጥሙ ኩነቶች ራሳቸውን ችለው የሚሰበሰቡና የሚያዙ መረጃዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይሁንና በሥርዓቱ ውስጥ ለሚወሰኑ ውሣኔዎች ውጤታማነት የጎላ ጠቃሚታ ሊኖራቸው የሚችሉት መረጃዎች ተለይተው በተቀመጡ ዓላማዎች ላይ ተመሥርቶ በጥንቃቄ የሚሰበሰቡና በስታትስቲክስ መልክ የሚደራጁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በመሆኑም የወንጀል ፍትሕ ሥርዓትን በተመለከተ የሚፈጠሩ ጠቃሚ መረጃዎች የሚሰበሰቡበት፣ የሚተነተኑበት፣ የሚያዙበት፣ የሚደራጁበት፣ የሚሰራጩበት እና ለሕዝብ ተደራሽ የሚሆኑበት ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

በፌዴራልና በክልል ደረጃ ያሉት የፍትሕ አካላት የወንጀል ፍትሕ ሥርዓትን የሚመለከቱ መረጃዎችን በተመጋጋቢነት፣ በተከታታይነት እና ወጥነት ባለው አሠራር ለመሰብሰብ፣ ለመተንተን፣ ለመያዝ፣ ለማደራጀት፣ እንዳስፈላጊነቱ ለማሰራጨት እና ለሕዝብ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችላቸውን አቅም ሊገነቡ ይገባል፡፡ ፍትሕ ሚኒስቴር የወንጀል ፍትሕ ሥርዓትን በተመለከተ

http://ethcriminalawnetwork.com

በየደረጃው የሚገኘውን የመረጃ አሰባሰብ ሥራዎች የመደገፍና ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመሆን ሀገር አቀፍ የመረጃ አሰባሰብ ሞዴል የመቅረፅ ግንባር ቀደም ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የወንጀል ምርመራ እና የዐቃቤ ሕግ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደትን ስለማሻሻል

### 3.1 የወንጀል ሕግን ማስፈፀም

የወንጀል ሕግን ማስፈፀም የወንጀል መከላከል አንዱ ገፅታ ሲሆን ሂደቱ ሊፈፀሙ የሚችሉ ወንጀሎችን ከማጥናትና ከመከታተል ጀምሮ የተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች ሪፖርት መቀበልን፣ የወንጀል ምርመራን፣ የክስ ምስረታን፣ የክርክርና የውሣኔ አሰጣጥ አሠራሮችን የሚያጠቃልል ሆኖ የወንጀል ቅጣትን ማስፈፀምና ከቅጣት በኋላ ታራሚን ከኀብረተሰቡ ጋር እስከ ማቀላቀል ያሉትን ሂደቶች ሁሉ ያካትታል፡፡

### 3.2 የሕዝብ ተሳትፎን ስለማጐልበት

የወንጀል ሕግን የማስፈፀም ተግባር ውጤታማ የሚሆነው የሚፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶችን ኀብረተሰቡ ሪፖርት ሲያደርግና የወንጀል ምርመራን ጨምሮ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ የሚሠሩ ሥራዎችን ሲያግዝ ነው፡፡ በዚህ ተግባር ኀብረተሰቡ ያለውን ሚና በአግባቡ መጫወት በወንጀል ምርመራ አሠራር እና በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ላይ የሚኖረውን አመኔታ በማሳደግ ረገድ ወሣኝ የሆነ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

በመሆኑም የወንጀል ፍትሕ ሥርዓትን አጠቃላይ የአፈፃፀም ብቃት እና ውጤታማነት ለማሣደግ የሚወሰዱ እርምጃዎች እንዲሁም የወንጀል ተጎጅዎችና ተጠርጣሪዎች ሚዛናዊ በሆነ አኳኋን የሚስተናገዱበትን አሠራር መዘርጋት ተገልጋዩ ኀብረተሰብ በሥርዓቱ ላይ ያለውን አመኔታ ያጎለብታል፡፡ በተጨማሪም የተፈፀሙ ወንጀሎች ሪፖርት የሚደረጉበት እና በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ የሚከናወኑ ሥራዎች ሰፊ የሕዝብ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡

በመሆኑም በየደረጃው የሚገኙ የወንጀል ፍትሕ አካላት ኀብረተሰቡ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ የሚያደርገውን ተሳትፎ የሚያበረታታና የሚያጎለብት እንዲሁም ሌሎች የሚጠበቅበትን አስተዋፆኦ ለማበርከት የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት መተግበር ይኖርባቸዋል፡፡

### 3.3 የመርማሪዎች እና የዓቃቤያነ ሕግን አቅም ማጐልበት

የሕግ የበላይነትን ለማስከበር ነፃና ገለልተኛ የዳኝነት አካል ከመኖሩ ጎን ለጎን በፍትሕ ሥርዓቱ የሕግ የበላይነትንም ሆነ ሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር ብቃት ያለው፣ የሰለጠነ እና በአግባቡ የተደራጀ የምርመራ እና የዐቃቤ ሕግ ተቋም ሊኖር ይገባል፡፡ ስለሆነም፡-

(ሀ) መርማሪዎች እና ዓቃቤያነ ሕግ የምርመራ እና የዐቃቤ ሕግ ተግባራቸውን በአግባቡ ለማከናወን እንዲችሉ የሙያ ዕውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውንና የሥነ ምግባር ደረጃቸውን የሚያሳድጉባቸውን ሥልጠናዎች እንዲያገኙ እንዲሁም ተግባሮቻቸውን በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችሏቸውን ዘመናዊ የምርመራ መሣሪያዎች በተቻለ መጠን እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡

(ለ) መርማሪዎች እና ዓቃቤያነ ሕግ ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ ከውስብስብና ከባድ የወንጀል ጉዳዮች አያያዝ፣ በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥና ውጭ ከሚገኙ አካላት ጋር በተፈለገው መልኩ ከመተባበር፣ ለወንጀል ድርጊት ጠቋሚዎች፣ ምስክሮችና ተጐጂዎች ተገቢውን ሕጋዊና ሰብዓዊ ጥበቃ ከማድረግ እና ከዓለም አቀፍ የፍትሕ አካላት ጋር ተገቢውን ትብብር ከማድረግ አንፃር ያላቸውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት በሚያስችላቸው ደረጃ አቅማቸው መገንባት ይኖርበታል፡፡

(ሐ) መንግሥት የመርማሪዎችንና የዐቃቤያነ ሕግን ልዩ የሙያ ብቃት በተከታታይ ለማሻሻል፣ ውስብስብ የወንጀል ጉዳዮችን የማስተናገድ አቅማቸውን ለማሳደግ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በመስኩ የሚደረገውን ትብብር ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚያስችል በወንጀል ምርመራ እና በዐቃቤ ሕግ የሙያ መስክ የመከካለኛና የረጅም ጊዜ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞችን አዘጋጅቶ ይተገብራል፡፡

(መ) በሥራ ላይ ያሉትም ሆኑ የሚወጡ ተዛማጅ ሕጎች የወንጀል ምርመራ ተግባርን በተፈለገው ደረጃ ውጤታማ ለማድረግና በምርመራ ተግባር ላይ የተሰማሩ መርማሪዎች እና ዓቃቤያነ ሕግ ሥራቸውን በተመለከተ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በተገቢው ደረጃ ለመከታተልና ለመገምገም በሚያስችል ሁኔታ መሻሻል እና መቀረፅ ይኖርባቸዋል፡፡

### 3.4 የወንጀል ምርመራ ዓላማ እና መርሆ

የወንጀል ምርመራ ገና ወደፊት ሊፈፀም በሚችል፣ ሊፈፀም በዕቅድና በዝግጅት ላይ በሚገኝ፣ አፈፃፀሙ ተጀምሮ ባልተጠናቀቀ ወይም አስቀድሞ በተፈፀመ የወንጀል ጉዳይ ላይ ሊደረግ ይችላል፡፡ የወንጀል ምርመራ በአጠቃላይ ስለ ወንጀል የማወቅ፣ ወንጀል እንዳይፈፀም የማስቆም፣ ወንጀሉ

ከተፈፀመ ጉዳቶችን የመቀነስ፣ የወንጀል ኢላማ የሆኑትን ሰዎች፣ ንብረቶች ወይም ጥቅሞችን የመከላከል፣ ወንጀል ፈፃሚዎችን ለሕግ የማቅረብ ወይም የወንጀል ተጎጂዎችን መብቶችና ጥቅሞችን የማስከበር ዓላማ ሊኖረው ይችላል፡፡

የወንጀል ምርመራ ተግባራት የወንጀል ጉዳዮች ላይ መረጃን ወይም ማስረጃን ማፈላለግን፣ ማግኘትን፣ መተንተንን፣ ማደራጀትን፣ ማኖርን፣ ለሚፈለገው ዓላማ ዝግጁ ማድረግን ወይም አግባብነት ላላቸው አካላት ማስረከብን የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡

የወንጀል ምርመራ ሂደት የሕግ የበላይነት፣ የፍትሐዊነት፣ የግልጽነት፣ የተጠያቂነት፣ ለሕዝብ ደህንነትና ሰላም ቅድሚያ የመስጠት፣ ለጉዳዮችና ለሁኔታዎች እንዲሁም ለጥቆማዎች ወቅታዊ ምላሽ የመስጠት እና በተጨባጭ ማስረጃ ላይ የተመሠረተ ሚዛናዊ ውሣኔ የመስጠት መርሆዎች ላይ የሚመሠረት ይሆናል፡፡

የወንጀል ምርመራ የሚካሄድባቸው ጉዳዮች፣ የወንጀል ምርመራ ዓላማ፣ ተግባራትና መርሆዎች የወንጀል ምርመራ ሥራዎችን ውጤታማ ለማድረግ በሚወጡ ወይም በሚሻሻሉ ተዛማጅ ሕጎችና የመርማሪዎችንና ዐቃቤያነ ሕግን ዝርዝር ተግባራት ለመወሰን በሚዘጋጁ መመሪያዎችና በሌሎች የአሠራር ሥርዓቶች ውስጥ በግልጽና በዝርዝር እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡

**3.5 <u>የወንጀል መርማሪዎች እና የዓቃቤያነ ሕግ ሚና</u>**

የወንጀል ምርመራ ሥራን በተመለከተ የመርማሪዎችና የዓቃቤያነ ሕግ ሚና በዋናነት የሚጠቀሱት የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) መርማሪዎች እና ዓቃቤያነ ሕግ የወንጀል ምርመራ ሥራ ውጤታማ እና ቀልጣፋ እንዲሆን ምርመራን በጋራ ያከናውናሉ፤ የምርመራ ሥራውን የመምራት እና የመከታተል ኃላፊነት የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይሆናል፡፡

(ለ) ማንኛውም መርማሪ ወይም ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ምርመራ ለመጀመር የሚያስችል በቂ መረጃ መኖሩን ካመነ በማንኛውም የወንጀል ጉዳይ ላይ ምርመራ መጀመር ይኖርበታል፡፡

(ሐ) ዐቃቤ ሕግ በማንኛውም የወንጀል ጉዳይ ላይ የወንጀል ምርመራ የማካሔድ ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የወንጀል ምርመራን አስመልክቶ ለሚመለከተው መርማሪ አካል አግባብ ያለው ትዕዛዝ የመስጠት እና የምርመራ ሂደትን ሕጋዊነት የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ ማንኛውም መርማሪ አካል ከወንጀል ምርመራ ጋር ተያይዞ በዐቃቤ ሕግ የሚሰጡ ትዕዛዞችንና ምክሮችን ተቀብሎ የመፈፀም ወይም የማስፈፀም ግዴታ ይኖርበታል፡፡

(መ) ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ምርመራ አካሔድን በሚመለከት የተሰበሰበውን ማስረጃና ጉዳዩ ለሕዝብ ጥቅም ያለውን ፋይዳ ከግምት በማስገባት በነፃነት፣ በተጠያቂነት፣ በፍትሐዊነትና በሕግ የበላይነት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ውሣኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡ የዐቃቤ ሕግ ውሣኔ ዋነኛ ዓላማ ክስ ከመመስረቱ በፊት ጉዳዩ በወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑን፣ ለፍርድ ቤት ቢቀርብ ተከሳሹን ጥፋተኛ ሊያደርገው የሚችል በቂ ማስረጃ እና የሕዝብ ጥቅም መኖሩን ማረጋገጥ ይሆናል፡፡

(ሠ) የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓትን ጨምሮ ሌሎች ተዛማጅ ሕጐች እና የአሠራር መመሪያዎች የምርመራ ሥራ የሚደራጅበትና የሚከናወንበት እንዲሁም መርማሪዎች እና ዓቃቤያነ ሕግ ሊኖራቸው ስለሚገባቸው ሚና በግልጽና በዝርዝር በሚያስቀምጥ ሁኔታ መቀረጽ ይኖርባቸዋል፡፡

## 3.6 <u>ውጤታማ እና ቀልጠፋ የምርመራ ሥርዓትን መፍጠር</u>

የወንጀል ምርመራ ሂደት ውጤታማና ሕጉን ተከትሎ በሚወጡ መመሪያዎች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማጠናቀቅ አስፈላጊነት ከሕዝብ ጥቅም እና በወንጀል ድርጊት ከተጐዱና ከተጠረጠሩ ሰዎች መብት አንፃር መታየት ይኖርበታል፡፡ በተለይም በወንጀል የተጠረጠረው ሰው በማረፊያ ቤት በሚገኝበት ጊዜ የምርመራውን ሥራ በአፋጣኝ የማጠናቀቅ ሁኔታ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ውጤታማ የወንጀል ምርመራ ሥራን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማከናወን እንዲቻል የመርማሪና የዐቃቤ ሕግ የወንጀል ጉዳዮች አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሥርዓት ወደ ወንጀል ፍትሕ ሂደቱ መግባት የማይገባቸው ጉዳዮች ወደ ሂደቱ እንዳይገቡ ለመከላከል፣ ወደ ሂደቱ የሚገቡና የተለያዩ ባሕርያት ያላቸው ጉዳዮች በሂደቱ ውስጥ በቀጣይነት ሊታዩ የሚችሉ ከማይችሉት በፍጥነት ለመለየት፣ ከሂደቱ መውጣት የሚገባቸውን በፍጥነት እንዲወጡና አፋጣኝ መፍትሔ እንዲያገኙ ለማድረግ እና በሂደቱ ውስጥ መቆየት የሚገባቸው ጉዳዮች ወደ ቀጣዩ የውሳኔ ደረጃዎች ሳይዘገዩ እንዲሸጋገሩ ለማድረግ እንዲሁም የወንጀል ምርመራ ሥርዓትን ፍትሐዊነት፣ ግልፅነትና ቀልጣፋነት በቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

በመሆኑም በተለያዩ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ምርመራዎችን አካሔዶ በተቀላጠፈና እና በጥራት ማጠናቀቅን በተመለከተ ተቋማዊ ግቦችን ማስቀመጥና ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራትን ለመከታተልና ለመገምገም በሚያስችል ደረጃ የአሠራር ሥርዓቶችን መፍጠር እንዲሁም የመርማሪዎች እና የዓቃቤያነ ሕግ አቅምን ማጎልበት ያስፈልጋል፡፡

### 3.7 የምርመራ ሥራ የሚጠናቀቅበትና ክስ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብ

የወንጀል ምርመራ የሚጠናቀቅበትና በጉዳዩ ላይ ክስ ማቅረብ የሚቻልበት የጊዜ ገደብ ሕጉን ተከትለው በሚወጡ መመሪያዎች ውስጥ እንደ ወንጀሉ ዓይነት፣ ክብደትና ውስብስብነት ተለያይተው የሚቀመጡ ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም መርማሪዎች እና ዓቃቤያነ ሕግ የምርመራ እና በጉዳዩ ላይ ክስ የማቅረብ ተግባራት በመመሪያዎች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መጠናቀቃቸውን የማረጋገጥ የጋራ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ዋስትና ተከልክለው በማረፊያ ቤት በሚገኙ ተጠርጣሪዎች ላይ መርማሪዎች ወይም ዓቃቤያነ ሕግ በሕጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምርመራውን ካለጠናቀቁ ወይም ክሱን ማቅረብ ካልቻሉ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት በሥነ-ምግባር ግድፈት ተጠያቂ የሚሆኑበት ጥብቅ ሥነ-ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ምርመራ እና የክስ አቀራረብ ሂደት የሚመሩባቸውን የአሠራር መመሪያዎች በማዘጋጀት በሥራ ላይ ያውላል፡፡

### 3.8 በወንጀል ምርመራ እና በዐቃቤ ሕግ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ ተግባራዊ የሚደረጉ የቁጥጥር ዘዴዎች

በሕግ የበላይነት በሚመራ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ መርማሪዎች እና ዓቃቤያነ ሕግ የሚያከናውኗቸው ተግባራት በተለይም በባሕርያቸው በግለሰብ መብቶች ላይ ጫና የሚያሳድሩ የእርምጃ ዓይነቶች እና በእርምጃዎቹ ላይ ሊደረጉ የሚገቡ ገደቦች በሕጉ ውስጥ በግልጽ ተለይተው ሊቀመጡ ይገባል፡፡

የመርማሪ እና የዐቃቤ ሕግ አሠራሮች በተለይም ከወንጀል ምርመራና ክስ ጋር በተያያዙ የሚከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ ውስጣዊ እና ውጫዊ የቁጥጥር ዘዴዎች በተገቢው ደረጃ ሊሻሻሉ እና ሊጠናከሩ ይገባል፡፡ የቁጥጥር ዘዴዎቹ የሚከናወኑት የመርማሪ እና የዐቃቤ ሕግ ተግባራት በግልጽነት፣ በተጠያቂነት፣ በፍትሐዊነት፣ በቅልጥፍና እና ውጤታማነት መርሆዎች መሠረት መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

### 3.9 የወንጀል ምርመራ የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

የወንጀል ምርመራ ሂደት የሚቋረጥባቸውን ሁኔታዎች በተመለከተ የሚወጡ ሕጐች የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች ባካተተ መልኩ ሊቀረጹ ይገባል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) ዐቃቤ ሕግ በሕግ ተለይቶ የተደነገገ በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያምን በመከናወን ላይ የሚገኝ የምርመራ ሂደት እንዲቋረጥ ማድረግ አለበት፡፡ ማንኛውም የወንጀል ምርመራ ወንጀሉ

http://ethcriminalawnetwork.com

በምኅረት ወይም በይርጋ ቀሪ ከሆነ፣ ቀደም ሲል ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ከሆነ፣ ወንጀል ስለመፈፀሙ አጠራጣሪ ሁኔታ ካጋጠመ ወይም ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ትዕዛዝ ከሰጠ ይቋረጣል፡፡

(ለ) በቀላል እሥራት ወይም በሕጉ መሠረት በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ እና በግለሰብ ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች በተበዳዩ እና በተጠርጣሪው መካከል እርቅ ከተፈፀመ በጉዳዩ ላይ እየተካሔደ ያለው ምርመራ ወይም ክስ በእነዚሁ አካላት አነሳሽነት ወይም ጠያቂነት ይቋረጣል፡፡

(ሐ) በዐቃቤ ሕግ ትዕዛዝ የተቋረጠ የወንጀል ምርመራ ለሂደቱ መቋረጥ ምክንያት ሆኖ የነበረው ሁኔታ በተለወጠ ወይም ቀሪ በሆነ ጊዜ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ትዕዛዝ ከተቋረጠበት እንዲቀጥል ወይም እንዲጀመር ሊደረግ ይቻላል፡፡

### 3.10 <u>በምርመራ መዛግብት ላይ የሚሰጡ ውሣኔዎች</u>

የወንጀል ምርመራን መዝገብ መርምሮ አግባብነት ያለው ውሣኔ የመወሰን፣ የክስ ቻርጅ የማዘጋጀት እና በተጠርጣሪው ላይ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ ሥልጣንና ኃላፊነት የዐቃቤ ሕግ ብቻ ይሆናል፡፡

ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ምርመራ መዝገብ መርምሮ የክስ ይመሥረት ወይም አይመሥረት ወይም የይዘጋ ውሣኔ በሚወስንበት ወቅት ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ቢቀርብ ተከሳሹን ጥፋተኛ ሊያደርገው የሚችል በቂ ማስረጃ እና የሕዝብ ጥቅም መኖር አለመኖሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

በግል የወንጀል ክስ ለመመሥረት በግል ተበዳይ አቤቱታ ከማያስፈልጋቸውና በሕገ መንግሥቱ በተቋቋሙ የሕግ አውጪ፣ የሕግ አስፈጻሚ ወይም የዳኝነት ተቋማት በባለሥልጠኖች ላይ ከሚፈፀሙ የስም ማጥፋትና የሐሰት የወንጀል ድርጊቶች በስተቀር በሌሎች በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎችን በተመለከተ ዐቃቤ ሕግ በጉዳዩ ላይ የተገኘ በቂ ማስረጃ መኖሩን ባመነ ጊዜ ተበዳዩ በራሱ ወጪና ኪሣራ የግል ክስ እንዲያቀርብ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

ዐቃቤ ሕግ ከወንጀል ጉዳይ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡትን ማስረጃዎች ለመመዘን፣ የሚያቀርባቸውን ክሶች ውጤታማነት እና ክሶቹም ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ክስ የማይመሰርትባቸው መስፈርቶች ጋር የሚጣጣሙ ስለመሆናቸው ለመወሰን የሚረዱትን የአሠራር መመሪያዎች ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

## 3.11 በወንጀል ጉዳይ ላይ ክስ ላለማቅረብ የሚሰጡ ውሣኔዎች

ዐቃቤ ሕግ የክስ አይመሥረት ወይም የይዘጋ ውሣኔ ለመስጠት መሠረት የሚያደርጋቸው ሕጋዊ ምክንያቶች በሕጉ በግልጽ ተዘርዝረው ሊቀመጡ ይገባል፡፡ እነዚህ የሚዘረዘሩ ሕጋዊ ምክንያቶች የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦችን የሚያካትቱ ይሆናሉ፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) ዐቃቤ ሕግ ተጠርጣሪውን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ የሆነ ማስረጃ የሌለ መሆኑን የተረዳው እንደሆነ፤

(ለ) ተጠርጣሪው በሌለበት ክሱ ሊታይ የማይቻል እንደሆነ፤

(ሐ) ተጠርጣሪው ያለመከሰስ ልዩ መብት ያለው ሆኖ ይህ መብቱ ያልተነሳ ከሆነ፤

(መ) ተጠርጣሪው የሞተ እንደሆነ፤

(ሠ) ተጠርጣሪው ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ዕድሜው በወንጀል የማያስቀጣው የነበረ እንደሆነ፤

(ረ) ተጠርጣሪው የተጠረጠረበት ጉዳይ ወንጀል ካልሆነ፤

(ሰ) ተጠርጣሪው የፈፀመው ወንጀል ቅድመ ሁኔታዎችን ሳይጥስ በይርጋ የታገደ ወይም ምኅረት ወይም ይቅርታ የተደረገለት ከሆነ፤

(ሸ) ተጠርጣሪው በወንጀሉ ከዚህ ቀደም ተከሶ ነፃ የወጣ ወይም የጥፋተኛነት ውሳኔ የተሰጠበት ወይም በፍርድ ቤት ጉዳዩ እየታየ ከሆነ፤

(ቀ) ተጠርጣሪው የተጠረጠረበት የወንጀል ድርጊት በወንጀል ሕግ የተፈቀደ ወይም የማያስቀጣና ይቅርታ የሚያሰጥ ከሆነ፤

(በ) ተጠርጣሪው ለተጠረጠረበት የወንጀል ድርጊት ፍፁም ኢ-ኃላፊ ስለመሆኑ በሕክምና የተረጋገጠ ከሆነ፤

ይሁንና ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች መሠረት የምርመራ መዝገቡን ለመዝጋት ምክንያት የሆነውን የሚያፈርስ ተቃራኒ ማስረጃ የተገኘ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ መዝገቡን እንደገና ማንቀሳቀስ ይቻላል፡፡

## 3.12 ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ክስ የማይመሠረትባቸው ጉዳዮች

ከላይ በተ.ቁ 3.11 ክስ ላለማቅረብ የተዘረዘሩት ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው ተጠርጣሪውን ጥፋተኛ ለማድረግ የሚያስችሉ በቂ ማስረጃዎች ቢኖሩም እንኳ የሚመሠረተው ክስ የሕዝብ ጥቅም

የማያስከብር መሆኑ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በታመነ ጊዜ ዐቃቤ ሕግ ክስ ላይመሠርት ይችላል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ክስ እንዳይቀርብ ለመወሰን የሚችልባቸው ሁኔታዎች በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉ እና በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በሚወጡ መመሪያዎች ውስጥ በዝርዝር ሊቀመጡ ይገባል፡፡ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ክስ የማይመሠረትባቸው ጉዳዮች የሚከተሉትን ዋና ዋና መስፈርቶችን መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) የተፈፀመው ወንጀል በጣም ቀላል መሆኑን ሕጉ በግልጽ በደነገገ ጊዜ እና ክሱ ቢመሠረት የሚወሰነው ቅጣት ተግሳጽ፣ ማስጠንቀቂያ፣ ወቀሳ መሆኑ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ከታመነ፣

(ለ) ተጠርጣሪው በዕድሜ መጃጀት ወይም በማይድን በሽታ በመያዙ ምክንያት ጉዳዩን በፍርድ ቤት መከታተል የማይችል የሆነ እንደሆነ፤

(ሐ) ወንጀሉ ከባድ ቢሆንም በተጠርጣሪውና በግል ተበዳይ መካከል የተፈጠረው የወንጀል ምክንያት በመደበኛ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ከሚሰጠው ውሣኔ ይልቅ በባሕላዊ ሕጎች እና ተቋማት ዘላቂ መፍትሔ ያገኛል ተብሎ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ከታመነ፤

(መ) ጉዳዩ በክስ ሂደት ውስጥ ቢያልፍ ብሔራዊ ደህንነትን ወይም የዓለም አቀፍ ግንኙነትን የሚጐዳ ይሆናል ተብሎ ከታመነበት፤

(ሠ) በቀላል እሥራት ወይም በሕጉ መሠረት በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ እና በግለሰብ ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች ሆነው በተበዳዩ እና በተጠርጣሪው መካከል እርቅ ተፈፅሞ ከሆነ፤

(ረ) የክስ መመሥረት ተመጣጣኝና ሚዛናዊ ያልሆነ የጉንዮሽ ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ፤

(ሰ) የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት በቀላል እሥራት የሚያስቀጣና ጉዳቱ አነስተኛ ሆኖ ተከሳሹ ጥፋቱን አምኖ ተበዳዩን ወይም ስለርሱ ባለመብቶች የሆኑትን በግልጽ ይቅርታ ከጠየቀ እና ያደረሰውን በደል መልሶ ለማስተካከል ዝግጁ ከሆነ፤

(ሸ) በማንኛውም ምክንያት ጉዳዩ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ሳይቀርብ በመቆየቱ ወቅታዊነቱን ወይም አስፈላጊነቱን ሲያጣ፤

(ቀ) የተፈፀመው ድርጊት በጣም ቀላል ወንጀል ከሆነ እና ጉዳቱ አነስተኛ ሆኖ ተጠርጣሪው ያደረገው ድርጊት የወንጀል ባሕርይ እንዳለው ፍፁም ከሆነ ግንዛቤ ማጣት ከሆነ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### 3.13 ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ክስ የሚመሠረትባቸው የወንጀል ጉዳዮች

በዚህ ፖሊሲ በቁጥር 3.12 ሥር ከተመለከተው በተቃራኒ በኢትዮጵያ ሕጐች እና ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው አለም ዓቀፍ ስምምነቶች ውስጥ በሰው ልጅ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ተብለው የተደነገጉትን የሰው ዘር በማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ በመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን በመሰወር ወይም ኢ-ሰብዓዊ ድብደባ በመፈፀም ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎችን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ ማስረጃ ካለ ዐቃቤ ሕግ ለሕዝብ ጥቅም ሲል ክስ የመመሥረት ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም እነዚህ የወንጀል ድርጊቶችን አስመልክቶ ዐቃቤ ሕግ የተጣለበትን ክስ ከመመሥረት ግዴታ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ዓይነት የሕግ ድንጋጌም ሆነ የአሠራር ሥርዓት በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ እንዳይኖር ማረጋገጥ የሁሉም የፍትሕ ሥርዓቱ ተቋማት የወል ኃላፊነት ይሆናል፡፡

### 3.14 ቅድሚያ ስለሚሰጣቸው የወንጀል ጉዳዮች

ዐቃቤ ሕግ ተጠርጣሪው በአንድ ድርጊት በርካታ ድንጋጌዎችን በመተላለፉ ወይም በርካታ ድርጊቶችን በመፈፀሙ ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን ተገቢ ያልሆነ የክሶች ቁጥር መብዛትና በዚህም የተነሳ በክርክር ወቅት ሊከሰት የሚችለውን ውስብስብ ሁኔታ ለመቀነስ ከፍተኛ ቅጣት በሚያስቀጡ ዋንኛ ድርጊቶች፣ በከባድ ወንጀሎች እና አደገኛ ባሕርይ ባላቸው ተጠርጣሪዎች ላይ ማተኮር ይኖርበታል፡፡ ክስ ሊመሠረትባቸው ከሚገቡ የወንጀል ጉዳዮች ቁጥር መብዛት የተነሣ በሁሉም ጉዳዮች ላይ እንደየአመጣጣቸው ክስ ለማቅረብ ባልተቻለ ጊዜ የወንጀሎቹን የተለየ ባሕርይና የሚያስከትሉትን ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት በተለይ በሕገ-መንግሥቱና በሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ የሚፈፀሙ፣ ሽብርተኝነት፣ ሙስና፣ በተደራጀ ቡድን የሚፈፀሙ፣ በሕፃናት እና በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ እና ለመሳሰሉት ከባድ ወንጀሎች ቅድሚያ በመስጠት ክስ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቅድሚያ ስለሚሰጣቸው የወንጀል ጉዳዮች የክስ ቅደም ተከተልን የሚመለከት በጥናት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት የሚዘረጋ ሲሆን ለዐቃቤያነ ሕግ የሚያገለግሉ ተዛማጅ የአሠራር መመሪያዎችም ያዘጋጃል፡፡

### 3.15 ስለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ልዩ ክትትልና ሥልጣን

ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በሕዝብ ሰላምና ደኅንነት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉትን በሕገ መንግሥትና በሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ የሚፈፀሙ፣ እንደ ሽብርተኝነት፣ የሀገር ክህደት፣ ከባድ የሰው ግድያ፣ ሙስና፣ እና በመሳሰሉት ከባድ ወንጀሎች ላይ የሚደረጉ ምርመራዎችን፣ የሚቀርቡትን ክሶችና የክርክር ሂደታቸውን በቅርብ ይከታተላል፤ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንደአስፈላጊነቱ መመሪያና ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

በተጨማሪም ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በተመረጡና የላቀ ሕዝባዊና ሀገራዊ ፋይዳ ባላቸው በሕገ መንግሥትና በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ወይም በመንግሥት የውጭ ደህንነትና በመከላከያ ኃይል ላይ የሚፈፀሙ፣ ዓለም አቀፍ ሕጎችን በመጣስ የሚፈፀሙ፣ የሽብርተኝነት ወይም ከባድ የውንብድና ወንጀሎች ላይ የምርመራ መዝገቦችን መርምሮ አግባብነት ያለው ውሣኔ መወሰን፣ ክስ ቻርጅ ማዘጋጀት እና በተጠርጣሪው ላይ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ መከራከር ይችላል፡፡

የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ልዩ ክትትል ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በሌሎች የወንጀል ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎችን በተመለከተ በተዋረድ ያሉ የዐቃቤያነ ሕግ ኃላፊነት የሚሆንበት አሠራር ይዘረጋል፡፡

## 3.16 <u>የማስረጃ ሕጋዊነት እና ማስረጃን ማሰባሰብ፣ ማኖርና በጥቅም ላይ ማዋል</u>

### 3.16.1 <u>ስለማስረጃ ሕጋዊነት</u>

በወንጀል ምርመራ ሂደት ውስጥ የሚሰበሰቡ ማስረጃዎች ሕጉን ተከትለው የተገኙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በሕገ ወጥ መንገድ ወይም በሕግ ከሰፈረው ሥርዓት ውጭ በመሔድ የተገኙ ማስረጃዎች በፍርድ ቤት ተቀባይነት የማይኖራቸው ወይም ዋጋ የሌላቸው ስለመሆኑ አግባብ ባለው ሕግ ውስጥ በግልጽ መስፈር ይኖርበታል፡፡ ከላይ የተቀመጠው ሁኔታ ቀሪ የሚደረግባቸው የተለዩ ጉዳዮች የሚኖሩም ከሆነ በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉ ውስጥ በግልጽ ተዘርዝረው ይቀመጣሉ፡፡

### 3.16.2 <u>ተጠርጣሪን ስለመያዝ፣ ስለማሰርና ብርበራ ስለማካሔድ</u>

ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር እንደማይገባ እና መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመበርበር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብት እንዳለው በሕገ መንግሥቱም ሆነ ሀገራችን ተቀብላ ባፀደቀቻቸው የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት እና ስምምነቶች ውስጥ በግልጽ ሰፍሮ ይገኛል፡፡

ይሁንና እነዚህ መብቶች ፍፁም ካለመሆናቸውም በተጨማሪ የሀገርን እና የሕዝብን ሰላምና ደህንነት እንዲሁም በሰዎች ነፃነትና መብቶች በሚፈፀሙት የወንጀል ድርጊቶች ምክንያት አደጋ ላይ እንዳይወድቁ ለመከላከል ሲባል በወንጀል ድርጊት የተጠረጠረን ሰው በሕግ ፊት አቅርቦ ፍትሐዊ ውሣኔ እንዲያገኝ ለማድረግ የሚያስችል ማስረጃ ለመሰብሰብ ሲባል አግባብ ያለው ሕግ በሚደነግገው ሥርዓት መሠረት መያዝ፣ ማሰርና መበርበር ይቻላል፡፡

በመሆኑም በወንጀል ድርጊት የተጠረጠረን ሰው በሕግ ፊት አቅርቦ ፍትሐዊ ውሣኔ እንዲያገኝ የሚያስችል ውጤታማ የወንጀል ምርመራ ለማካሔድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ አግባብነት ያላቸው ሕጐች በሚያስቀምጡት ሥርዓት መሠረት እና ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ተጠርጣሪውን ለመያዝ፣ ለማሰርና ለመበርበር የሚያስችል አሠራር በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

ስለሆነም የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በሚያግዝ መልኩ የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) በሕጉ በግልጽና በዝርዝር የተቀመጠ አስቸኳይ ወይም አስገዳጅ ሁኔታ ካላጋጠመ ወይም የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ካልሆነ በስተቀር መርማሪ እና ዐቃቤ ሕግ ከፍርድ ቤት ተገቢውን ፈቃድ ሳያገኙ ማንኛውንም ሰው ለመያዝ፣ ለማሰር፣ መኖሪያ ቤቱን፣ ሰውነቱንና ንብረቱን ለመበርበር የማይችሉ መሆኑን፤

(ለ) በወንጀል ጉዳይ ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው የምርመራ ወይም የክስና የፍርድ ሂደት እስከሚጠናቀቅ ድረስ በዋስ ሊለቀቅ የማይችል ከሆነ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ የሚደረግ ሲሆን የቆይታውም ጊዜ እንዳይረዝምና የምርመራው ወይም የክስና የፍርድ ሂደቱ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ የሚመለከታቸው አካላት ሂደቱን የማፋጠን ግዴታ እንዳለባቸው፤

(ሐ) ኅብረተሰቡንና ግለሰቦችን ሊከሰት ከሚችለው ጉዳት ለመጠበቅ ወይም ተጠርጣሪው የቀረበበትን ክስ በሚፈለገው መልኩ እንዲከታተል ለማድረግ ሲባል የወንጀል ክስ የቀረበበት ተከሳሽ የክሱ ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ በዐቃቤ ሕግ ጠያቂነት በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ሊያዝ እንደሚችል፤

(መ) ማንኛውም በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ጉዳዩ በፍርድ ቤት ተሰምቶ የጥፋተኝነት ውሳኔ እስኪወሰን ድረስ ከፍርደኞች ተለይቶ እንዲቆይ እና ተጠርጣሪ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች ከአዋቂ ተጠርጣሪዎች ተለይተው እንዲያዙ እንደሚደረግ፤

(ሠ) በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ከምርመራ ወይም ከፍርድ ሂደት መጠናቀቅ ጋር በተያያዘ በእሥር ላይ የሚቆዩ ተጠርጣሪዎችን ወይም ተከሳሾችን ቁጥር ለመቀነስ እንዲቻል የምርመራ ወይም የፍርድ ሂደት የሚቀላጠፍበትን ሁኔታዎች ከማመቻቸት በተጨማሪ ከእሥር ውጭ ያሉ ሌሎች አማራጮችን በሥራ ላይ ለማዋል የሚቻልባቸውን መንገዶች

ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ማጥናትና መተግበር እንዳለባቸው እና የመሳሰሉት ይሆናሉ፡፡

### 3.16.3 የወንጀል ፍሬን ስለማገድ እና ስለመውረስ

በወንጀል ጉዳይ ውጤታማ ክስ ለማቅረብ በምርመራ ወቅት ከወንጀሉ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ንብረቶች ማገድ እና መያዝ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡ በተለይም በንብረት ወይም በገንዘብ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመከላከል፣ ወንጀል ለመፈፀም በጥቅም ላይ የዋለ ወይም የወንጀል ፍሬ የሆነ ንብረትን ገንዘብን ለማገድና ለመያዝ እንዲሁም የሚጠረጠሩ የሂሣብ ሠነዶችን ለመመርመር የሚያስችሉ የሕግና የአሠራር ሥርዓቶች በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ሥራ ላይ መዋል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ አሠራር እንደ ሽብርተኝነት፣ የሙስና እና በተደራጁ ቡድኖች የሚፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመዋጋት ያስችላል፡፡ በመሆኑም የወንጀል እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጐች ይህንኑ አሠራር በተግባር ላይ ለማዋል በሚያስችል መልኩ ሊሻሻሉና ሊቀረፁ ይገባል፡፡ እነዚህ የሚሻሻሉም ሆነ በአዲስ መልክ የሚወጡ ሕጐች የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮችን በሚያካትት መልኩ መቀረፅ ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) የወንጀል ፍሬ የሆነ ንብረትን ወይም ገንዘብን መያዝን፣ ማገድ፣ መውረስና ማስተዳደር እንደሚቻል፤

(ለ) የወንጀል ፍሬ ማንኛውም ወንጀልን በመፈፀም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተገኘ የኢኮኖሚ ጥቅም ሲሆን ወንጀሉ ከተፈጸመ በኋላ በተከታታይነት የተቀየረ፣ ዋጋው እንዲጨምር የተደረገ፣ የተለወጠ ወይም የተቀላቀለ ንብረትን እንዲሁም ከዚሁ ንብረት የተገኘ ገቢን፣ ካፒታልን ወይም ሌላ የኢኮኖሚ ጥቅምን እንደሚጨምር፤

(ሐ) በሕዝብ ሰላምና ደኅንነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉትን በሕገ መንግሥትና በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ላይ፣ እንደ ሽብርተኝነት፣ የሀገር ክህደት፣ ሙስና፣ ከባድ የሰው ግድያ፣ ከባድ የውንብድና እና በውስጥ ወይም በውጭ የሀገር ደህንነት ላይ ጉዳት በሚያደርስ ወንጀል ተጠርጥሮ የተከሰሰ የማንኛውም ሰው የግል ንብረት ወይም ገንዘብ እንደሚያዝ ወይም እንደሚታገድ እንዲሁም በሌለበት ጥፋተኛ ሆኖ ከተፈረደበት ከሚወሰንበት ከማንኛውም ቅጣት ጋር የግል ንብረቱ እንደሚወረስ ማድረግ እና የመሳሰሉት ጉዳዮች ናቸው፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com

### 3.17 ልዩ የምርመራ ዘዴዎች አስፈላጊነት

ከጊዜ ወደ ጊዜ ከባድ፣ ውስብስብ እና ዓለም አቀፋዊ ባሕርይ ያላቸውን የወንጀል ድርጊቶች ለመከላከል እና አፈፃፀማቸውን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ ለማውጣት እንዲቻል ዘመናዊ የሆኑ የምርመራ ቴክኒኮችን በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ማስተዋወቅና አሠራሩንም አግባብ ባላቸው ሕጎች የተደገፈ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በወንጀል ምርመራ ሂደት በሕግ ዕውቅና ከሚሰጣቸው ልዩ የምርመራ ቴክኒኮች እና ዘዴዎች መካከል በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች እና ሌሎች መንገዶች ማስረጃዎችን መሰብሰብና በስውር ክትትል ማድረግ፣ ማንነትን ደብቆ ወይም በሌላ ሽፋን የተደራጁ የወንጀል ቡድኖች ውስጥ ሠርጎ መግባት፣ የተለያዩ የይምሰል ሕጋዊ ግንኙነቶችን ከተጠርጣሪው ጋር በመፍጠር ወይም በማከናወን ማስረጃ ማሰባሰብ እና የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

በዘመናዊ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ እነዚህ የምርመራ ዘዴዎች እጅግ በጣም አስፈላጊ ሲሆኑ በተለይም በተደራጁና በታጠቁ ቡድኖች በሚፈፀሙ፣ ውስብስብ የሆነ የኢኮኖሚ እና የሙስና ወንጀሎችን ለመዋጋትና አጥፊዎችን ለሕግ ለማቅረብ ወሣኝ ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡

እነዚህ ውስብስብና ልዩ የሆኑ የምርመራ ዘዴዎች በጥቅም ላይ እንዲውሉ ሲደረግ አብረው ሊነሱ የሚችሉ የሕግ ጉዳዮችን የወንጀል ሕግጋት በበቂ ሁኔታ መልስ ሊሰጡ ይገባል፡፡ በመሆኑም ማሻሻያ የሚደረግባቸውና የሚወጡ የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተካተቱትን እና በሕገ መንግሥቱ መሠረት ዕውቅና ያገኙትን የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችንና በተለይም በወንጀል የተጠረጠሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎችን መሠረታዊ መብቶች በሚያረጋግጥ መልኩ ከላይ የተጠቀሱትን ልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴዎች ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል አኳኋን ሊቀረፁ ይገባል፡፡

#### 3.17.1 ሠርጎ መግባትና ክትትል ስለማድረግ

ሠርጎ በመግባት እና ክትትል በማድረግ የሚከናወኑ የወንጀል ምርመራ ሥራዎችን በሚመለከት የወንጀል እና ሌሎች ተዛማጅ ሕጎች ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጉዳዮች በያዘ መልኩ ሊሻሻሉና በአዲስ መልክ ሊቀረፁ ይገባል፡፡

በዚህም መሠረት ከባድና መካከለኛ ወንጀል የተፈፀመ ወይም እየተፈፀመ ወይም ሊፈፀም የታቀደ ስለመሆኑ ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ካለ በሕጉ ሥልጣን ከተሰጠው ኃላፊ አስቀድሞ በሚገኝ ፈቃድ መሠረት የወንጀል መርማሪዎች ወይም እነርሱ የወከሏቸው ሰዎች፡-

(ሀ) በወንጀሉ በተጠረጠሩ ቡድኖች ወይም ድርጅቶች መካከል ሠርጐ በመግባት ስለወንጀሉ አፈፃፀም የሚያሳዩ ማስረጃዎችን መሰብሰብ፤ ወይም

(ለ) በወንጀሉ ላይ ጠቃሚ የሆኑ ማስረጃዎችን ለመሰብሰብ በተጠርጣሪዎች ላይ በድብቅ ክትትል ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

የሰርጐ መግባትን እና የክትትል ተግባራትን ዝርዝር አፈፃፀም እንዲሁም በሰርጐ መግባት ተግባር ላይ የተሰማራው መርማሪ ወይም እርሱ የወከለው ሰው ከሰርጐ መግባት ተግባር ጋር በተያያዘ ለሚፈፅማቸው የተወሰኑ የወንጀል ድርጊቶች ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ የሚሆንበት ሁኔታዎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች ውስጥ በዝርዝር ይደነገጋሉ፡፡

### 3.17.2 <u>የግል መገናኛ ዘዴዎችን መጥለፍ</u>

የግል ህይወት እና ግላዊነት የመከበር መብት ጋር ተያይዞ ግለሰቦች የትኛውንም የመገናኛ ዘዴ በመጠቀም የሚያደርጉትን ግንኙነት መጥለፍ የማይቻል ስለመሆኑ በሕገ መንግሥታችን ውስጥ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ሰዎች ከጠበቃቸው፣ ከኃይማኖት አባታቸው፣ ከትዳር ጓደኛቸው እና ከሐኪማቸው ጋር የሚያደርጓቸው ግንኙነቶች ካልሆኑ በስተቀር የሕዝቡን ሰላምና ደኅንነት ለመጠበቅ እና ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት ሲባል ለሚደረግ የወንጀል ምርመራ የግለሰቦችን ማናቸውንም የግል የመገናኛ ዘዴዎች በዘርፉ በሚወጡ ዝርዝር ሕጎች መሠረት መጥለፍ ይቻላል፡፡

ስለሆነም የግል የመገናኛ ዘዴዎች ሊጠለፉ የሚችሉት በወንጀል ጉዳይ ላይ ለሚደረግ ምርመራ ውጤታማነት ወይም ሊፈፀም የተቃረበን ከባድ የወንጀል ድርጊት ለማስቆም ሲባል የመገናኛ ዘዴውን መጥለፍ አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳምን በቂ ምክንያት ለፍርድ ቤቶች ሲቀርብላቸው በሚሰጡት ትዕዛዝ ላይ በመመሥረት ነው፡፡

### 3.17.3 <u>ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የግል መገናኛ ዘዴዎች የሚጠለፉባቸው ሁኔታዎች</u>

የግል የመገናኛ ዘዴዎችን መጥለፍ የሚፈቀደው ከላይ እንደሠፈረው በፍርድ ቤት በሚሰጥ ትዕዛዝ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሕዝቡን ሰላምና ደህንነት ከማስጠበቅ አንፃር በሚከተሉት ልዩ ሁኔታዎች ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የግል የመገናኛ ዘዴዎችን መጥለፍ እንደሚቻል አግባብነት ባላቸው ሕጐች ውስጥ መካተት ይኖርበታል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) እንደ ሕገ መንግሥትን እና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ወይም የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ከፍተኛ አደጋ ላይ የሚጥል የሽብርተኝነት ወይም የሙስና ወይም በሌላ ሰው ሕይወት እና ንብረት ላይ ከባድ ጉዳት የሚያስከትል ወንጀል ስለመፈፀሙ ወይም የሚፈፀም ስለመሆኑ

በቂ ጥርጣሬ ሲኖር እና አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ሥልጣን ያለው የበላይ ኃላፊ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት መርማሪዎች እና ዐቃቤያነ ሕግ የተጠርጣሪዎችን የግል የመገናኛ ዘዴዎችን መጥለፍ ይችላሉ፡፡

(ለ) ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አሥራ አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከባድ ወንጀል ስለመፈፀሙ ወይም እየተፈፀመ ስለመሆኑ ወይም ሊፈፀም የተቃረበ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ካለው፣ አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥምና ወንጀሉን በተመለከተ በሌላ መንገድ ማስረጃ ለማግኘት የማይቻል መሆኑን ባመነ ጊዜ የምርመራ አካላት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማናቸውንም የተጠርጣሪ የግል የመገናኛ ዘዴዎችን እንዲጠልፉ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

(ሐ) ከላይ በፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" ሥር በተገለፁት ሁኔታዎች ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የግል የመገናኛ ዘዴዎችን የመጥለፍ ተግባር እንዲፈፀም መነሻ የሆኑ ማስረጃዎችና ምክንያቶች በጽሑፍ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኘሬዝዳንት ወይም ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዝዳንት በአጭር ጊዜ መቅረብና መጽደቅ ይኖርባቸዋል፡፡

### 3.17.4 የወንጀል መረጃን ለሚያቀብሉ ሰዎች እና ወኪሎች የሚደረግ ጥበቃ

አንዳንድ የወንጀል ዓይነቶች በባሕርያቸው በቀላሉ ማስረጃ የማይገኝባቸው ከመሆናቸው የተነሣ የሕግ አስፈፃሚ አካላትና ባለሙያዎች ወንጀል ፈፃሚዎችን በሕግ ፊት አቅርቦ ለማስቀጣት እንዲቻላቸው በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ከተጠርጣሪዎቹ ጋር ግንኙነት በመፍጠራቸው ምክንያት እየተመረመረ ስላለው የወንጀል ድርጊት መረጃ ማግኘት የሚችሉ ሰዎችን እንደ ወሣኝ መረጃ ወይም የማስረጃ ምንጭ አድርጐ ይቆጥሯቸዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ሰዎች በአግባቡ ተጠቅሞ ወንጀለኞችን በሕግ ፊት ለማቅረብ ይቻል ዘንድ በወንጀል ጉዳይ ላይ ለመርማሪ አካላት መረጃ ለሚያቀብሉ ሰዎችና ለወኪሎቻቸው የሚያበረታታ አስፈላጊው የሕግ ጥበቃ ማድረግ በሚያስችል መልኩ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሕጎች እንደገና ሊቀረፁ ይገባል፡፡

### 3.17.5 በወንጀል ተካፋይ የነበረን ተጠርጣሪ ከክስ ነፃ ስለማድረግ

ለወንጀል ተግባር በተቋቋሙ ቡድኖች፣ በረቀቀ የወንጀል አፈፃፀም ዘዴዎች ወይም በትጥቅ በመታገዝ ወይም በርካታ ሰዎች ተሳታፊ በሆኑባቸው የአመፅ ተግባሮች አማካይነት በተፈፀሙ ወንጀሎች ውስጥ ተካፋይ የነበረ ተጠርጣሪ ሌሎች ተጠርጣሪዎችን የሚመለከቱና በጉዳዩ ላይ ለሚደረገው የምርመራና የክስ ሂደት ውጤታማነት ጠቀሜታ ያላቸውን ማስረጃዎች ለመስጠት ፈቃደኛ በሆነ ጊዜ ዐቃቤ ሕግ ለሂደቱ ተባባሪ የሆነውን ተጠርጣሪ የተጠያቂነት ደረጃ ዝቅ እንዲል

ወይም እንደሁኔታው ከክሱ ሙሉ በሙሉ ነፃ እንዲሆን ሊወስን የሚችልበት አሠራር ወይም ሁኔታ በወንጀል ሥነ ሥርዓቱ እና በሌሎች ተዛማጅ ሕጎችም ውስጥ መካተት ይኖርበታል፡፡

በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ የተፈለገውን ውጤት ያስገኛል ብሎ ካመነ በሚከተሉት ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ተጠርጣሪን ከክሱ ነፃ ማድረግ የሚችል መሆኑ በወንጀል እና በሥነ ሥርዓት ሕጎች ውስጥ በግልጽ ሊቀመጥ ይገባል፡፡ እነሱም፡-

(ሀ) ምርመራ የሚደረግበት ወንጀል በአፈፃፀም ደረጃው እና በሚያስከትለው የቅጣት መጠን ከባድ ሊባል የሚችልና በተለይም በተደራጁ ቡድኖች፣ የጦር መሣሪያን በመጠቀም ወይም እንደ ሙስና እና ሽብርተኝነት ዓይነት ሆነው በረቀቀ ስልት የሚፈፀሙ ወንጀሎች ሲሆን እና

(ለ) ከወንጀሉ ውስብስብነት የተነሣ በድርጊቱ ተካፋይ የነበረውን ተጠርጣሪ ትብብር ማግኘት ካልተቻለ በስተቀር ጉዳዩን በምርመራ ለማውጣት እና ውጤታማ ክስ ለማቅረብ የማይቻል ወይም አዳጋች ሲሆን ናቸው፡፡

ከላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ድርጊት ውስጥ ተካፋይ የነበረ ተጠርጣሪ በሌሎች ተጠርጣሪዎች ላይ በፍርድ ቤት በምስክርነት በሚቀርብበት ወቅት እንደአስፈላጊነቱ ለምስክሮች ከሚሰጥ ልዩ ጥበቃ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው አስፈላጊ የሆኑ ጥበቃዎች እንደሚያገኝ አግባብነት ባላቸው ሕጎች እና መመሪያዎች ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፡፡

### 3.18 ስለቀዳሚ ምርመራ

ዐቃቤ ሕግ ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ የተሰበሰቡ አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑና የማስረዳት ዋጋቸው ከፍ ያሉ ማስረጃዎች በአግባቡ መያዛቸውን የማረጋገጥና አግባብ ያላቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች የመውሰድ ኃላፊነት አለበት፡፡ በመሆኑም እነዚህ የተጠቀሱትን ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመወጣት በሚያስችል ሁኔታ የወንጀል ሥነ ሥርዓት እና ሌሎች ተዛማጅ ሕጎች ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ጉዳዮች ባካተተ መልኩ ሊሻሻሉ ወይም በአዲስ መልክ ሊቀረፁ ይገባል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) ከላይ ከሰፈረው ኃላፊነት ጋር በተያያዘ ዐቃቤ ሕግ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር የሚወድቁና በተለይም ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ መጣል፣ ሽብርተኝነት፣ ሙስና፣ በተደራጁ ቡድኖች የሚፈፀሙ፣ ከባድ የነፍስ ግድያ እና ከባድ የዘረፋ የወንጀል ጉዳዮች ላይ በቀጥታ ክስ ለመመሥረት ካልወሰነ በስተቀር

የተሰበሰቡት የሰውና ሌሎች ተያያዥ ማስረጃዎችን ደኅንነት ለማስጠበቅ ሲባል በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀዳሚ ምርመራ ማድረግ እንደሚያስፈልግ፤

(ለ) ቀዳሚ ምርመራ አድራጊው ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ ያቀረባቸውን ማስረጃዎች በአግባቡ ተጠብቀው መቆየታቸውን እና መደራጀታቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ በዝርዝር መዝግቦ ማስቀመጥ እንዳለበትና ቀዳሚ ምርመራ በሚደረግበት ወቅት ተከሳሹም በበኩሉ ያሉትን ማስረጃዎች እንዲመዘገቡለት ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላል የሚሉ ናቸው።

### 3.19 የምስክሮች ጥበቃ

በአንዳንድ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ተዓማኒነት ያለው ምስክር በመጥፋቱ ወይም ጉዳዩን በሚገባ የሚያውቁ ምስክሮች ፍርድ ቤት ቀርበው ለመመስከር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ምክንያት ብቻ ውጤታማ ክስ ማቅረብ ሳይቻል ይቀራል። ምስክሮቹ የወንጀል ድርጊቱን ፈፃሚና ስለአፈፃፀሙ በሚገባ እያወቁ በምስክርነት ለመቅረብ እምቢተኛ ከሚሆኑባቸው ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው በቀልን በመፍራት ወይም ማስፈራሪያ እየተደረገባቸው ስለሚሆን ነው።

አብዛኛውን ጊዜ ለወንጀል ድርጊቶች ቁልፍ ምስክር ሆነው የሚቀርቡት ራሳቸው የወንጀሉ ተጎጅዎች በመሆናቸው ምክንያት ለምስክሮች የሚደረግ ጥበቃ ለእነሱም በተመሳሳይ መልኩ እንደሚያስፈልግ ይታወቃል። በመሆኑም ለምስክሮች የሚደረገው ጥበቃ የወንጀል ተጎጅዎች ምስክር ሆነው በሚቀርቡበት ጊዜ እንደአግባብነቱ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ በሚፈፀሙ ከባድና አደገኛ የሆኑ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ሚዛናዊና ውጤታማ ክስ ማቅረብ እንዲቻል ለጥቃት የተጋለጡ ምስክሮችን ለመርዳትና ሥጋታቸውን ለማስወገድ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ተገቢ ይሆናል።

በመሆኑም ለወንጀል ምስክሮች የሚደረግ ጥበቃን አስመልክቶ በዘርፉ የሚወጡ ሕጎች የሚከተሉትን ፍሬ ጉዳዮች በዋናነት መያዛቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። እነዚህም፡-

(ሀ) ለምስክሮች የሚደረግ ጥበቃ ውጤታማ እና ተጨባጭ እንዲሆን በወንጀል ምርመራ ሂደት ወቅት ከሚደረገው ጥበቃ በተጨማሪ በጉዳዩ በፍርድ ሂደት ላይ እያለ እና እንዳስፈላጊነቱ የፍርድ ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ባሉት ጊዜያት ተፈፃሚ ሲሆን ይገባል።

(ለ) ለምስክሮች ከሚደረጉ የተለያዩ የጥበቃ ዓይነቶች መካከል ለምስክሩ ቀጥታ የአካልና የንብረት ደህንነት ጥበቃ ማድረግ፣ የምስክሩን ማንነት መለወጥ እና በሚስጥር ተደብቆ እንዲቆይ ማድረግ፣ እንዲሁም ጉዳዩ በፍርድ መሰማት ሂደት ላይ እያለ የምስክሩን ቃል በቪዲዮ አማካይነት ለችሎት እንዲቀርብ ወይም ጉዳዩ በዝግ ችሎት እንዲታይ ማድረግን

http://ethcriminalawnetwork.com

እና የመሳሰሉትን በዋናነት መጥቀስ የሚቻል ሲሆን አጠቃላይ ዓላማውም ከወንጀል ጋር በተያያዘ ምስክር በመሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሚሳተፉ ሰዎች ሁለንተናዊ ጥበቃ በማድረግ የወንጀል ድርጊቶችንና ፈፃሚዎችን እንዲጋለጡ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የወንጀል ሕግን ማስፈፀም ነው፡፡

(ሐ) ለምስክር የሚደረግ ጥበቃ አስፈላጊነት የጥበቃው ዓይነት እና የቆይታው ጊዜ፣ ምስክሩ በወንጀል ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ምስክርነት የሕዝብ ጥቅምን ከማስከበር አኳያ በሚያስገኘው ጠቀሜታ ላይ ተመስርቶ ሊመዘን ይገባል፡፡ እነዚህ የጥበቃ ርምጃዎች በተለይም በሕገ መንግሥቱና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ፣ እንደ ሙስና፣ ሽብርተኝነት እና በተደራጁ ቡድኖች በሚፈፀሙ ወንጀሎች ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

(መ) ለምስክሮች የሚደረገው ጥበቃ ዝርዝር አፈፃፀምን በተመለከተ በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግና በሌሎችም ተዛማጅ ሕጐች ውስጥ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡

(ሠ) ለምስክሮች የሚደረግ ጥበቃ አፈፃፀምን በተመለከተ አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ የሚውሉ ሲሆን ለሚመለከታቸው መርማሪዎች እና ዓቃቤያነ ሕግ አስፈላጊው ሥልጠና ይሰጣል፡፡

## 3.20 <u>ስለ ኤግዚቢት አያያዝና አስተዳደር ሥርዓት</u>

ውጤታማ፣ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋ፣ ተገማችና የሕዝብ አመኔታ ያለው የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ለመገንባት ሊከናወኑ ከሚገቡ በርካታ ተግባራት መካከል ከኤግዚቢት አያያዝ፣ አስተዳደርና ውሣኔ አሰጣጥ አንፃር ግልጽ የሕግና የአሠራር ሥርዓቶችን መፍጠር አንዱ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ውጤታማ፣ ፍትሐዊና ቀልጣፋ የኤግዚቢት አያያዝና አስተዳደር ሥርዓት ለመገንባት የሚከተሉት መሠረታዊ ጉዳዮች አግባብነት ባላቸው ሕጎች ውስጥ በግልጽና በዝርዝር መካተት ይኖርባቸዋል፡፡

እነዚህም፡-

(ሀ) ኤግዚቢት ከወንጀል ድርጊት ጋር ተያይዞ ያለ ፍሬ ነገርን ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል በተለያዩ ዘዴዎች የሚቀርብ ማንኛውም ግዙፋዊ ነገር ሲሆን በዋናነት ሠነድን፣ ድምጽን፣ ምስልን፣ ዳታን ወይም ማንኛውም ዓይነት ማስረጃን የያዘ ቁስን እንደሚያጠቃልል፤

(ለ) በልዩ ሁኔታ በሕግ በግልጽ ካልተደነገገ በስተቀር ያለ ፍርድ ቤት የብርበራ ወይም የመያዥ ትዕዛዝ በማንኛውም መንገድ ኤግዚቢት መያዝ እንደማይቻል፤

(ሐ) ለኤግዚቢቱ መያዝ ምክንያት የሆነው የወንጀል ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ እስኪያገኝ ድረስ የተያዘው ኤግዚቢት የሚቆየው መርማሪው ጋር እንደሚሆን፤

(መ) በሕጉ መሠረት የተያዘው ኤግዚቢት ለጊዜው እንደተያዘ ንብረት የሚቆጠር ሲሆን ኤግዚቢቱ ለሚቀርበው ክስ ያለው አግባብነት ላይ የመወሰን ሥልጣን የዐቃቤ ሕግ መሆኑን፤

(ሠ) የተያዘው ኤግዚቢት ክሱን ለማስረዳት አቅም የሌለው መሆኑን፣ በሕጉ መሠረት የማይወረስ ወይም የማይወድም መሆኑን ወይም በወንጀል ፍሬነት የተያዘ ሆኖ ለባለቤቱ ሊመለስ የሚችል መሆኑን ዐቃቤ ሕግ ካመነ ኤግዚቢቱ ለባለቤቱ እንዲመለስ መወሰን እንደሚችል፤

(ረ) በተያዘው ኤግዚቢት ላይ የባለቤትነት ወይም የባለይዞታነት ክርክር በሰዎች መካከል ከተነሳ ኤግዚቢቱ በተያዘበት ጊዜ የኤግዚቢቱ ባለቤት ወይም ባለይዞታ ለነበረ ሰው መመለስ እንደሚገባ፤ ኤግዚቢቱ በሚያዝበት ጊዜ ትክክለኛ ባለቤቱ ወይም ባለይዞታው ማን እንደሆነ ለማወቅ የማይቻል ከሆነ ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩ የፍትሐብሔር መፍትሔ እንዲያገኝ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ እንዳለበት፤

(ሰ) የተያዘው ኤግዚቢት በሕግ መሠረት የሚወረስ ወይም የሚወድም፣ ግዙፍነት ያለውና ለአያያዝ አስቸጋሪ የሚበላሽ ለማቆየት ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትል ወይም በሌሎች ምክንያቶች ለማቆየት የማይቻል ከሆነ የኤግዚቢቱን ናሙና፣ ምስል፣ ድምጽ፣ ቪዲዮ ቪዥዋል ወይም በሌላ ምቹ ዘዴ ምትክ ማስረጃ እንዲኖር በማድረግ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ኤግዚቢቱ እንዲወረስ፣ እንዲወድም፣ በገበያ ዋጋ እንዲሸጥ፣ ለባለቤቱ እንዲመለስ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መፍትሔ እንዲያገኝ ማድረግ እንደሚያስፈልግ፤ ወይም

(ሸ) ኤግዚቪት የሚያዝበትንና የሚተዳደርበትን እንዲሁም ዐቃቤ ሕግ አግባብነት ያለው ውሣኔ የሚወስንበትን ዝርዝር የአሠራር ሥርዓቶችን ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መዘርጋት እንዳለበት የሚሉ ናቸው፡፡

## 3.21 የዋስትና ጉዳዮች

### 3.21.1 የዋስትና ጥያቄን ለመቀበል ሊተኮርባቸው የሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች

በወንጀል ተጠርጥረው በተያዙ ሰዎች የሚቀርቡ የዋስትና ጥያቄዎች ላይ ፍርድ ቤቶች ውሣኔ በሚሰጡበት ወቅት ሊያተኩሩባቸው የሚገቡ ዋና ዋና ጉዳዮች በወንጀል ሥነ ሥርዓት እና በሌሎች ተዛማጅ ሕጐች ውስጥ በግልጽ ተዘርዝረው ሊደነገጉ ይገባል፡፡ ከእነዚህም መካከል የዋስትና ጥያቄ የቀረበበት የወንጀል ጉዳይ ከባድነት፣ የተጠርጣሪው ያለፈ የወንጀል ሪከርድ እና የግል ፀባይ፣ በዋስትና ጥያቄው ላይ የሚሰጠው ውሣኔ በሕዝብ ጥቅም ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ፣ ተጠርጣሪው በዋስትና ቢለቀቅ በተፈለገ ጊዜ ፍርድ ቤት ተመልሶ ሊቀርብ የሚችል ስለመሆኑ ወይም ሌላ ወንጀል ሊፈጽም የሚችል ስለመሆኑ ወይም ምስክሮችን በማስፈራራትና ማስረጃን በማጥፋት በፍትሕ አሰጣጡ ላይ እክል ሊፈጥር የሚችል ስለመሆኑ እና የመሳሰሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በፍርድ ቤት የሚሰጠው ዋስትና እንደተጠበቀ ሆኖ መርማሪዎች እና ዓቃቤያነ ሕግ በቀላል እሥራት በሚያስቀጣ ወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ ሰዎች በተፈለጉ ጊዜ በሕግ ፊት ይቀርባሉ ብለው ካመኑ ፍርድ ቤት ከመቅረባቸው በፊት በዋስ ሊለቋቸው የሚችሉበት ሥነ ሥርዓት አግባብነት ባላቸው ሕግጋት ውስጥ በግልጽ እና በዝርዝር ይደነገጋል፡፡

### 3.21.2 በቅድመ ሁኔታዎች በዋስ ስለመለቀቅ

ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በዋስ ለመለቀቅ ሊያቀርብ ስለሚገባው ዋስትና በተለይም ግለሰቡ በራሱ ዋስትና ወይም ተጨማሪ ዋስ በማቅረብ መለቀቅ የሚገባው ስለመሆኑ እና ከዋስትናው ጋር ተያይዘው ስለሚቀመጡ ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች በሕጉ ውስጥ በግልጽ ሊደነገጉ ይገባል፡፡

ሕጉ ከዋስትና ጋር ተጣምረው ስለሚቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች በተለይም የተለቀቀው ሰው የዋስትና ግዴታው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ለአንድ የመንግሥት አካል በቋሚነት ሪፖርት እንዲያደርግ፣ ወደተወሰኑ ሥፍራዎች እንዳይደርስ፣ ከተወሰነ አካባቢ እንዳይርቅ፣ ከአንዳንድ ድርጊቶች እንዲቆጠብ ወይም ከተበዳይ ወይም ከምስክር ጋር እንዳይገናኝ ትዕዛዝ መስጠት ስለሚቻልባቸው ሁኔታዎች በግልጽ ሊደነግግ ይገባል፡፡

#### 3.21.3 በሕግ ዋስትና የማያሰጡ የወንጀል ዓይነቶች

ማንኛውም በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው በዋስ የመለቀቅ መብቱ የተረጋገጠለት ቢሆንም የሕዝብንና የሀገርን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በልዩ ሁኔታዎች በሕግ ሊገደብ ይችላል። ስለሆነም በዋስትና መብት ላይ ገደብ የሚጥሉ ልዩ ሁኔታዎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች በግልጽ ተዘርዝረው ሊደነገጉ የሚገባ ሲሆን ድንጋጌዎቹም በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው በማንኛውም ሁኔታ የዋስትና መብቱ የማይከበርለት መሆኑን በግልጽ ማካተት ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም አሥራ አምስት ዓመት እና ከዚያ በላይ ሊያስቀጡ የሚችሉ ወንጀሎች ሆነው በሕገ መንግሥትና በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ላይ የተፈፀሙ፣ የሙስና፣ በተደራጀ ቡድን የተፈፀሙ፣ የዘር ማጥፋት፣ የሰው ዘር ላይ የተፈፀሙ፣ የአስገድዶ መድፈር እና በሕፃናት ላይ የተፈፀሙ የወሲብ ጥቃት ወንጀሎች ተጠርጥሮ የተያዘ ማንኛውም ሰው የዋስትና መብት እንደማይኖረው በግልጽ በሕጋችን ውስጥ ይካተታል።

ከላይ የተመለከተው ቢኖርም በጉዳዮች አስፈላጊነትና ወቅታዊነት ላይ በመመሥረት በሕግ ዋስትና የማያሰጡ የወንጀል ዓይነቶች፣ የወንጀል ቅጣት ጣራ ወይም ወለል በየጊዜው ሊሻሻል ይችላል።

### 3.22 ዓለም አቀፍ ትብብር

#### 3.22.1 ጠቅላላ

የወንጀል ጉዳዮችን በሚመለከት የሚደረግ ዓለም አቀፍ ትብብር በይዘቱ እጅግ ውስብስብ እየሆነ ከመምጣቱም በላይ ሂደቱም በሕግ አስፈፃሚ አካላት እና በሕግ ተርጓሚው አካል ላይ የሚጥለው ኃላፊነት ከፍተኛ ነው።

ከላይ የተጠቀሱት አካላት በሙሉ በዓለም አቀፍ ትብብር መስክ ድርሻቸውን በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ እና ሀገሪቱም ከወንጀል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚጠበቁባትን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች በአግባቡ መወጣት እንድትችል ሙያዊ ብቃታቸውን ማሣደግ አስፈላጊ ነው።

#### 3.22.2 የዓለም አቀፍ ትብብር ዓይነቶችና አፈፃፀማቸው

ከወንጀል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የዓለም አቀፍ ትብብር የሚደረግባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች የተመሠረቱ የወንጀል ክሶችን፣ ዓለም አቀፍ ባሕርያት ባላቸው ወንጀሎች ላይ የሚደረጉ ምርመራዎችንና ለወንጀል ድርጊት ምስክሮችና ተጐጂዎች የሚደረጉ ጥበቃዎችን

በተመለከተ የሚደረጉ ትብብሮች እንዲሁም ለፍርድ ቤት ውሣኔዎች ዕውቅና መስጠትና ማስፈፀም፣ የወንጀል ጉዳዮችን ወደሌላ ሀገር ማስተላለፍ፣ አሳልፎ መስጠት፣ የጋራ የሕግ ድጋፍ እና የወንጀል ፍሬ የሆኑ ንብረትን ወይም ገንዘብን ማገድና መውረስን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

የዓለም አቀፍ ትብብር መሠረት የሚያደርገው ሀገሪቷ የተቀበለቻቸው የዓለም አቀፍ ሕጎችና መርሆዎች ወይም የሁለትዮሽ ወይም ከብዙ ሀገሮች ጋር የሚደረጉ ስምምነቶች ወይም እንደሁኔታው የሀገሪቷ ሕጎች ሊሆን ይችላል፡፡

በመስኩ ያሉ ተዛማጅ ሕጎች የዓለም አቀፍ ትብብር የሚመራባቸው ዘመናዊ አሠራሮችን፣ መርሆዎችንና ሕጎችን በሚያካትቱ እና አፈፃፀማቸውንም በሚያቀላጥፍ መልኩ ሊሻሻሉና አዳዲስ ድንጋጌዎች እንዲያካትቱ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሕግ አስፈፃሚ አካላትና ባለሙያዎች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያከናውኗቸው ተግባራት ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውና ደረጃውን በጠበቀ አሠራር ለመሥራት በሚያስችላቸው ሁኔታ አቅማቸውን መገንባት ያስፈልጋል፡፡

የዓለም አቀፍ ትብብርን የሚመለከቱ ጥያቄዎች አቀራረብና አፈፃፀማቸው በዋናነት በኢትዮጵያ የዲፕሎማሲያዊ የግንኙነት መስመር አማካይነት የሚከናወኑ ቢሆንም በጉዳዩ ዓይነትና ለግንኙነቱ መሠረት በሆኑ ሕጐችና ስምምነቶች ላይ ተመሥርቶ በቀጥታ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነት መፍጠር የሚቻልባቸው የሕግና የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ በተጨማሪም ከላይ የተጠቀሱ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው በሀገር ውስጥ እና በሀገር ውጭ የሚከናወኑ ተዛማጅ ተግባራትን የማስተባበሩ ኃላፊነት የፍትሕ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## የወንጀል ፍትሕ ሂደቱን ውጤታማነትና ፍትሐዊነት ስለማሻሻል

### 4.1 ጠቅላላ

በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ከሚስተናገዱት የወንጀል ጉዳዮች ቁጥር መጨመር እና ከፍርድ አሰጣጥ ሂደቱ መራዘም ጋር ተያይዞ በሚፈጠረው የመዝገብ ክምችት ሳቢያ የሚከሰተውን የፍትሕ መዘግየትና ተጠርጣሪዎች ለረጅም ጊዜ በማረፊያ ቤት እንዲቆዩ የሚደረግበትን ሁኔታ ለማስቀረት አስፈላጊው የአሠራር እና የሕግ ማሻሻያ ሊደረግ ይገባል፡፡

በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ የሚስተዋለው አላስፈላጊ የሆነ የፍርድ አሰጣጥ ሂደት መራዘም የተነሳ በሰዎች መብት ላይ የሚከሰተውን ተገቢ ያልሆነ ጫና ለማስቀረት እንዲሁም በምስክሮች አለመገኘት እና በማስረጃ መጥፋት ምክንያት የሚፈጠረውን የወንጀል ክሶች ውጤታማ አለመሆን

ችግር ለማስወገድ የሚያስችሉ የተለያዩ መፍትሔዎች በግልጽ ተለይተው ሊቀመጡ ይገባል፡፡ ከእነዚህም መፍትሔዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

(ሀ) ዘመናዊ የወንጀል ጉዳዮች አያያዝ ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፤

(ለ) የተቀላጠፈ የፍርድ አሰጣጥ ሂደትን ተግባራዊ ከማድረግ በተጨማሪ እጅ ከፍንጅ እና እንደሁኔታው ሌሎች የወንጀል ጉዳዮች በተፋጠነ የወንጀል ፍትሕ አሰጣጥ ሂደት የሚታዩበትን ሥርዓት ማጠናከር፤

(ሐ) ተከራካሪ ወገኖች ያሏቸውን ማስረጃዎች የክስ መሰማት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት እንዲያስታውቁ ማድረግ፤ ተጠርጣሪዎች ቀደም ብለው ጥፋተኝነታቸውን እንዲያምኑ የሚያበረታታና የጥፋተኝነት ድርድር የሚካሔድበት የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ፤

(መ) በወንጀል ፍትሕ ሂደት ላይ ጫና እያሳደሩ ያሉትን የወንጀል ጉዳዮች ለመቀነስና እነዚህንም በአግባቡ ለማስተናገድ እንዲቻል አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች ተግባራዊ የሚደረጉበትን ሥርዓት መዘርጋት፤

(ሠ) በፍትሕ ሥርዓቱ ጉልህ ድርሻ ያላቸውን የተከላካይ ጠበቆች ሙያን፣ አመለካከትና ሥነ ምግባርን ማጎልበት፤ በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች በአግባቡ መወከላቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ነፃ የሕግ ምክር አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበትን ሥርዓት መዘርጋት፤

(ረ) የይግባኝ ሥርዓትን ከማጠናከር ባሻገር ያላግባብ ጥፋተኛ የተባሉ ሰዎች ካሣ ማግኘት የሚችሉበትን ሥርዓት መዘርጋት፤

(ሰ) የዐቃቤያነ ሕግ እና የምርመራ አካላትን አቅም ማጐልበት፤

(ሸ) የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱን አፈፃፀም በመከታተልና በመገምገም ውጤቱን ለሚመለከታቸው አካላት መግለጽ የሚሉ ናቸው፡፡

## 4.2 <u>የወንጀል ጉዳዮችን አያያዝ ዘመናዊ ስለማድረግ</u>

### 4.2.1 <u>ጠቅላላ</u>

በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ የጉዳዮችን ፍሰት እና የፍትሕ አካላትን ግንኙነት ለማሻሻል፣ ዘመናዊ የወንጀል ጉዳይ አያያዝ ስልትን ተግባራዊ ለማድረግና የጉዳዮች አያያዝን በዘመናዊ

http://ethcriminalawnetwork.com

የግንኙነትና የመረጃ ቴክኖሎጂ ለመደገፍ የሚያስችሉ አሠራሮች ተቀርፀው ተግባራዊ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

የመረጃ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የወንጀል ጉዳዮችን ፍሰት እና እንቅስቃሴ መከታተል የጉዳዮችን አያያዝ ዘመናዊ በማድረግ ረገድ ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ በወንጀል ጉዳዮች አያያዝ ሥርዓት ውስጥ ሊተኮርበት የሚገባው ዋና ነጥብ የተለያዩ የወንጀል ጉዳዮች የፍርድ ሂደታቸው እንዳይጓተት በተለያዩ መደቦች በመከፋፈል የተለያዩ የመፍትሔ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው እና በልዩ ሥርዓቶች ውስጥ እንዲያልፉ ማድረግ ነው፡፡ ይህም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የወንጀል ጉዳዮችን ቀልጣፋና ቀላል በሆነ ዘዴ ለመለየት የሚያስችሉ አሠራሮችን የሚጨምር ይሆናል፡፡

የፍርድ ሂደትን እንደዋና የመፍትሔ አቅጣጫ ከመጠቀም ይልቅ ከፍርድ ሂደት በፊት ጉዳዮች የሚፈቱበት እና ተጠርጣሪዎች ጥፋተኝነታቸውን የሚያምኑበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

### 4.2.2 <u>የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን</u>

የደንብ መተላለፍ ወንጀሎችን አስመልክቶ በክልሎች ሕግ የማውጣት፣ የመተርጎም እና የማስፈፀም ሥልጣን የክልል መንግሥታት ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን ለክልል ፍርድ ቤቶች፣ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ለተሰጣቸው አካላት እና እንደሁኔታው ደንቡን ላወጣው አስፈፃሚ አካል እንዲሆን በሕግ ይደነገጋል፡፡ ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱት አካላት የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች በቀላል ሥርዓት የሚታዩበትን አሠራር የመዘርጋት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

## 4.3 <u>የተቀላጠፈ እና የተፋጠነ የፍርድ አሰጣጥ ሂደት ስለሚመራበት ሥነ-ሥርዓት</u>

### 4.3.1 <u>ጠቅላላ</u>

በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ክርክር ዓላማ በተጠርጣሪ ላይ የቀረበውን ክስና ማስረጃ እንዲሁም የተከሳሹን የመከላከያ ማስረጃ በማመዛዘን ፍትሐዊ ውሣኔ መስጠት ነው፡፡ በወንጀል ጉዳዮች ላይ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሣኔ ተጠርጣሪውን በነፃ ማሰናበት ወይም የጥፋተኝነት ውሣኔ በመስጠት ቅጣት መጣል ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ውሳኔዎችን ሊያካትት ይችላል፡፡ በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ክርክር ቀጥታ ክስ፣ ይግባኝ፣ ሰበር እና የመጨረሻ ውሣኔ እንደገና ማየትን ያካትታል፡፡ የፍትሕ ሥርዓቱን ውጤታማነት ለማረጋገጥ እና የፍትሕ አካላቱን የሰው ኃይልና ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል፣ የተራዘሙ ቀጠሮዎችን እና የችሎት ጊዜያትን በተቻለ መጠን መቀነስ የሚያስችል የሕግና የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

#### 4.3.2 ተከሳሽ ወይም ምስክር ፍርድ ቤት ስለማቅረብ

በወንጀል ጉዳይ ላይ የሚሰጡ አላስፈላጊ ቀጠሮዎችን ለመቀነስና የፍርድ ሂደቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የተከሳሾችና ክሱን ለማስረዳት የተጠሩ ምስክሮች ክሱ በሚሰማበት ዕለት በችሎት መገኘታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ በሥራ ላይ ያሉ እና በመስኩ የሚወጡ ሕጎች የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች በሚያካትት መልኩ ሊሻሻሉና ሊቀረፁ ይገባል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ ወይም ምስክር የሆኑ ሰዎች ፍርድ ቤት የሚቀርቡት በፍርድ ቤት በሚሰጥ መጥሪያ መሠረት መሆኑን፤

(ለ) መርማሪዎች እና ዐቃቤያነ ሕግ ከፍርድ ቤት በሚሰጥ መጥሪያ መሠረት ተከሳሽን እና ምስክሮችን በችሎት የማቅረብ ኃላፊነት እንዳለባቸው፤

#### 4.3.3 ቀልጣፋ የወንጀል ክርክር ስለሚመራበት ሥነ-ሥርዓት

በማንኛውም የወንጀል ክስ ጉዳይ የተሟላ ማስረጃ እስከቀረበ ድረስ ማንኛውም የወንጀል ክርክር በተቀላጠፈ ሥነ ሥርዓት ሊመራ ይችላል፡፡ ቀጠሮ ለመስጠት የሚያስገድድ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር የፍርድ ውሣኔ የሚሰጠው ወዲያውኑ መሆን ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ፍትሕዊ ውሳኔ ለመስጠት ይረዳ ዘንድ ተጨማሪ ጊዜ መውሰድ አስፈላጊ መሆኑ ሲታመን ፍርድ ቤቱ በራሱ ወይም በተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ ቀጠሮ መስጠት ይችላል፡፡ ክርክር የሚካሔድበትና ውሣኔ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ እንደወንጀሉ ክብደት እና ውስብስብነት ሊለያይ በሚችል መልኩ አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች ውስጥ በግልጽ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

#### 4.3.4 በተፋጠነ የወንጀል ፍትሕ አሰጣጥ ሂደት የሚታዩ የወንጀል ጉዳዮች አያያዝ

##### 4.3.4.1 መርህ

በሕገ መንግሥቱና በሌሎች ተዛማች ሕጎች ውስጥ የተደነገጉት የተከሳሽ መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው ለወንጀል ክሶች በተፋጠነ መንገድ ውሣኔ ለመስጠት፣ በፍትሕ አካላቱ ላይ የሚፈጠረውን የሥራ ጫና ለመቀነስ፣ ማስረጃዎች ክሱን የማስረዳት ብቃታቸው ሳይቀንስ በትኩሱ እንዲቀርቡ ለማድረግ፣ ከኤግዚቢት ጋር ተያይዘው ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት እና የተጎጅዎችንና የተጠርጣሪን መብቶችን በአግባቡ ለማስከበር እንዲቻል የእጅ ከፍንጅ እና ከነዚሁ ጋር በተመሳሳይ

ሥርዓት ሊታዩ የሚችሉ ሌሎች የወንጀል ጉዳዮች በተፋጠነ የወንጀል ፍትሕ አሰጣጥ ሂደት የሚታዩበትን ሥርዓት በመዘርጋት በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

#### 4.3.4.2 የተፋጠነ የወንጀል ፍትሕ አሰጣጥ ሂደት የሚመራበት ሥነ-ሥርዓት

ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፍትሕ አካላት በማስረጃ ይዘታቸው ውስብስብነት የሌላቸው የእጅ ከፍንጅ እና ሌሎች ወንጀሎች በተፋጠነ የወንጀል ፍትሕ አሠጣጥ ሂደት ወዲያውኑ ለፍርድ ቤት ቀርበው ፍትሐዊ ውሳኔ የሚያገኙበትን አሠራር ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

የእጅ ከፍንጅ እና ሌሎች የወንጀል ጉዳዮች በተፋጠነ የፍትሕ አሰጣጥ ሂደት እንዲታዩ የመወሰን ሥልጣን የዐቃቤ ሕግ መሆኑን እና ይህን ውሳኔ ለመወሰንም የወንጀሉን አጠቃላይ ባሕርይ፣ የማስረጃዎቹን ይዘትና ብቃት፣ እንዲሁም የተጠርጣሪውንና የተጎጅውን ፍላጎት ከግምት በማስገባት መሆን እንዳለበት በወንጀል ሥነ ሥርዓትና በሌሎች ተዛማች ሕጎቻችን ውስጥ በግልጽ ይደነገጋል፡፡

### 4.4 የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሽ ስለሚዛወርበት ሁኔታ

ማንም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሊሰኝ የሚችለው ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ በሚያቀርበው ማስረጃ ጥፋተኝነቱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ይሁንና ተከሳሹ በሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ላይ አደጋ ማድረስ፣ እንደ ሽብርተኝነት፣ ሙስና ወይም በተደራጁ ቡድኖች በተፈፀሙ ወንጀሎች የተከሰሰ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ የማስረዳት ሸክምን ወደ ተከሳሽ ለማዛወር የሚችል መሠረታዊ ፍሬ ነገሮችን ካስረዳ የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሹ ሊዛወር የሚችልበትን ሥርዓት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች ውስጥ ይካተታሉ፡፡

### 4.5 ማስረጃን ስለመግለጽ፣ ጥፋተኝነትን ስለማመን እና የጥፋተኝነት ድርድር

#### 4.5.1 ጠቅላላ

የወንጀል ጉዳዮች ወደ መደበኛ የክርክር ሂደት ውስጥ ከመግባታቸው በፊት መፍትሔ የሚያገኙበትን እንደ ጥፋተኝነት ድርድር ያሉ አሠራሮችን በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ በማካተት የሥርዓቱን የቀልጣፋነት፣ የውጤታማነትና የፍትሐዊነት ደረጃ ከፍ ማድረግ ይቻላል፡፡ በመሆኑም እነዚህን አሠራሮች ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጉዳዮች አግባብነት ባላቸው ሕጎችና መመሪያዎች ውስጥ በግልጽ መስፈር ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህም:-

(ሀ) ዐቃቤ ሕግ እና ተከሳሹ ወይም ጠበቃው የፍርድ ሂደቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ማስረጃዎቻቸውን እርስ በእርስ እንዲለዋወጡ ማድረግ፤

(ለ) የጥፋተኝነት ድርድር የሚካሔድበትን የሕግ ማዕቀፍ በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ማካተት፤

(ሐ) የዐቃቤ ሕግን ክስ የማንሣት ወይም የክስ ሂደቱን የማቆየት ወይም የማቋረጥ ሥልጣንን በሕግ ውስጥ በግልጽ ማካተት የሚሉ ናቸው፡፡

### 4.5.2 <u>ማስረጃ ስለማስታወቅ ወይም ስለመግለጽ</u>

በወንጀል ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ ክርክሮችና የክስ ማሰማት ሂደቶችን ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሐዊ በሆነ አሠራር እንዲካሔዱ ለማድረግ የክርክር ሂደቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ዐቃቤ ሕግና ተከሳሽ በቀረበው ክስ ላይ ያሏቸውን ማስረጃዎች እርስ በእርስ ለመለዋወጥ የሚያስችላቸው የሕግ ማዕቀፍ በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የዚህ የሕግ ማዕቀፍ መኖር ተከሳሽ ቀደም ብሎ ጥፋተኝነቱን እንዲያምንና ከዐቃቤ ሕግ ጋር የጥፋተኝነት ድርድር እንዲካሔድ ወይም ሌሎች ከመደበኛ የክርክር ሂደት ውጭ ያሉ የመፍትሔ እርምጃዎች ተግባራዊ እንዲደረጉ ያግዛል፡፡

በመሆኑም ማስረጃ ማስታወቅን ወይም መግለጽን አስመልክቶ በወንጀል ሥነ ሥርዓት እና በሌሎች ተዛማጅ ሕጎች ውስጥ የሚከተሉት ጉዳዮች በግልጽ መደንገግ ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) ዐቃቤ ሕግ የክስ መሰማት ሂደት ከመጀመሩ በፊት ለተከሳሹ የክስ መከላከያ ሊሆን የሚችለውን ጨምሮ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ክሱን ለማስረዳት የተሰበሰበውን ማንኛውም ማስረጃ ለተከሳሽ የመግለጽ ግዴታ እንዳለበት፤

(ለ) ዐቃቤ ሕጉ የሚገልፃቸው ማስረጃዎች የክስ መሰማት ሂደት ከመጀመሩ በፊት በቀጥታ ለተከሳሽ ማድረስ የፍርድ ሂደቱን ፍትሐዊነት ሊያጓድል፣ በምስክሮችና በሌሎች ማስረጃዎች ወይም በሕዝብ ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ ይችላል ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት ካለ እነዚህን ጉዳቶች ለመከላከል የሚያስችል ሌሎች የማስረጃ አገላለጽ ሥነ-ሥርዓቶችን በመጠቀም ማስረጃዎችን መግለጽ እንዳለበት፤

(ሐ) በዐቃቤ ሕግ የሚገለጸው ማስረጃ ተከሳሹ የቀረበበትን ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረበበትን ምስክር የመጠየቅ፣ ራሱን ለመከላከል የሚያስችል ማስረጃን የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሩ ቀርቦ እንዲሰየምለት የመጠየቅ መብቱን ለማስከበርና ለማረጋገጥ በሚያስችል ቅርፅና ይዘት መሆን እንዳለበት፤ እና

(መ) ተከሳሽ የክስ መሠማት ሂደት ከመጀመሩ በፊት ለክሱ መከላከያ መሠረት የሚያደርጋቸውን ማስረጃዎችንና የሕግ ድንጋጌዎችን ለዐቃቤ ሕግ በዝርዝር የመግለጽ ግዴታ እንዳለበት፣ የሚሉ ናቸው፡፡

### 4.5.3 ማስረጃን ማስታወቅ ወይም መግለጽ ቀሪ ስለሚሆኑባቸው ልዩ ሁኔታዎች

ከላይ በተራ ቁጥር 4.5.2 ሥር የተመለከቱት ቢኖሩም ዐቃቤ ሕግ የመሠረተውን ክስ ለማስረዳት የሚጠቀምበት ካልሆነ በስተቀር ዐቃቤ ሕጉ የሚከተሉት ልዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት ማስረጃን ለተጠርጣሪ ወይም ለተከሳሽ ማስታወቅ ወይም መግለጽ የለበትም፡፡

(ሀ) ማስረጃው ሊፈፀም የሚችል ወይም የተፈፀመ ወንጀልን ለማጥናት፣ ለመከታተል፣ ለመከላከል ወይም ለመመርመር የሚውል ዘዴን፣ ቴክኒክን፣ የአሠራር ሥነ-ሥርዓቶችን ወይም የተግባር መመሪያዎችን የሚመለከት ከሆነ እና የማስረጃው መገለጽ ለወንጀሉ መፈፀም ወይም ለተጠርጣሪዎቹ ከሕግ ማምለጥ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ይሆናል ተብሎ ከታመነበት፤

(ለ) በተጠርጣሪው ላይ የሚመሠረተው ክስ ገና በዝግጅት ላይ ያለ ወይም የክስ መሰማት ሂደት ገና ያልተጀመረ ከሆነ እና የማስረጃው መገለጽ ክሱን ሊያሰናክል፣ የፍትሕ መጨናገፍን ሊያስከትል ወይም የፍርድ ሂደቱን ነፃነትና ገለልተኝነት ሊያዛባ የሚችል ከሆነ፤

(ሐ) ማስረጃው በሕግ ጥበቃ ከሚደረግላቸው ልዩ መብቶች ጋር የሚገናኝ ከሆነ እና የዚህ ልዩ መብት ተጠቃሚ ሰው መብቱን ላለመጠቀም በግልጽ ያላስታወቀ ከሆነ፤

(መ) ማስረጃው የሀገር መከላከያን፣ ፀጥታንና ደኅንነትን ወይም አለም ዓቀፍ ግንኙነትን የሚመለከት ከሆነ እና አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ምስጢር ተብሎ የተመደበ ከሆነ፤

(ሠ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሕዝበ በይፋ እንዲገለጽ ከወሰነው በስተቀር ማስረጃው በማንኛውም የምክር ቤቱ ወይም ለምክር ቤቱ ውሣኔ በተላከ ሠነድ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ፤ እና

(ረ) ማስረጃው የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ወይም የፋይናንስ ደህንነትን የሚመለከት ከሆነ እና አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ምስጢር ተብሎ የተመደበ ከሆነ የሚሉ ናቸው፡፡

በዚህ ቁጥር በፊደል ተራ "ለ" ሥር የተመለከተው ማስረጃ ያለመግለጽ ግዴታ የክስ መሰማት ሂደቱ ሲጀምር ቀሪ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ክስ መሰማት ሂደቱ ከተጀመረ በኋላ ማስረጃውን የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com

### 4.5.4 የጥፋተኝነት ድርድር እና ጥፋተኝነትን ስለማመን

#### 4.5.4.1 የጥፋተኝነት ድርድር ዓላማና አካሔድ

በወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች ድርጊቱን አስቀድመው ማመናቸው የሁሉም የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ አካላት ፍላጐት ከመሆኑም በላይ የወንጀል ፍትሕ ሂደቱን የአፈፃፀም ብቃት ደረጃ ከፍ እንደሚያደርግ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የጥፋተኝነት ድርድር ሥርዓት መኖር በመደበኛው የክርክር እና የክስ ሂደት ወቅት የሚወጣውን ወጪና የሚባክነውን ጊዜ ይቀንሳል፤ እንዲሁም በወንጀል ፍትሕ አካላቱ ላይ የሚፈጠረውን የወንጀል ክሶች ብዛትና የሥራ ጫና ለመቀነስ ዓይነተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ድርድር የሚደረግበት ጉዳይ በመደበኛ የፍርድ ሂደት ውስጥ በማለፉ ምክንያት በተጎጅዎች፣ በምስክሮችና በተከሳሾች ሥነ ልቦና ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለማስቀረት የሚያስችል ሲሆን በድርድሩ ሂደት ተከሳሹ ለፈፀመው ጥፋት በራሱ ነፃ ፍቃድ ኃላፊነት የሚወስድ ስለሆነ ባደረገው ድርጊት ተፀፅቶ በመታረም ለወደፊቱ ሰላማዊ ሆኖ እንዲኖር ያስችላል፡፡

#### 4.5.4.2 የጥፋተኝነት ድርድር አሠራርን ለመዘርጋት ሕጎችን ስለማሻሻል

የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግን ጨምሮ ሌሎች ተዛማጅ ሕጐች ጥፋተኝነትን ስለማመን የሚደረገውን ድርድር በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ በግልጽ ለማካተትና አፈፃፀሙንም በአግባቡ ለመምራት በሚያስችል መልኩ ተሻሽለው እንዲቀረፁ የሚደረግ ከመሆኑም በላይ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በተጠርጣሪው እና በዐቃቤ ሕግ መካከል የሚደረገውን የጥፋተኝነት ድርድር ውጤታማና ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ለመምራት የሚያስችል ዝርዝር መመሪያ አዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ሕጎች እና መመሪያዎች የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች ማካተት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) የድርድር ሂደቱን የማካሔድ እና ከድርድሩ የሚገኘውን ስምምነት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት በማቅረብ ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ እንዲፀድቅ እና በስምምነቱ መሠረት ተፈፃሚ እንዲሆን የማድረግ ኃላፊነት የዐቃቤ ሕግ እንደሚሆን፤

(ለ) ዐቃቤ ሕግ በማንኛውም ወንጀል የተጠረጠረ ሰው ለፍርድ ቤት አቅርቦ ለማስቀጣት የሚያስችል ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ የተጠርጣሪው ጠበቃ ባለበት ድርድር ማካሔድ እንደሚችል እና ከድርድሩ የሚገኘው ማንኛውም ስምምነት በጽሑፍ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ካልፀደቀ በስተቀር ተፈፃሚ እንደማይሆን፤

(ሐ) በዐቃቤ ሕግ እና በተጠርጣሪው መካከል የሚካሔድ የጥፋተኝነት ድርድር በማንኛውም ምክንያት ያለስምምነት ቢቋረጥ ወይም በተካሔደው ድርድር የተደረሰው ስምምነት ለፍርድ ቤት ቀርቦ በማንኛውም ምክንያት ተቀባይነት ቢያጣ በተካሔደው ድርድር ምክንያት የተገኘ ማንኛውም ማስረጃ ለድርድሩ ምክንያት የሆነው የወንጀል ድርጊት የተፈፀመው በተጠርጣሪው መሆኑን ለማስረዳት በየትኛውም የፍርድ ሂደት ላይ መቅረብ የማይችል መሆኑን እና ከቀረበም በሕግ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ፤

(መ) በዐቃቤ ሕግ እና በተጠርጣሪ መካከል የሚደረገው የጥፋተኝነት ድርድር በክስ ብዛት ወይም በቅጣት መጠን ወይም በፍሬ ነገር ወይም በሦስቱም ላይ ሊሆን እንደሚችል የሚሉ ናቸው፡፡

#### 4.5.4.3 ጥፋተኝነትን ስለማመን

ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ ተቀብሎ ድርጊቱን መፈፀሙንና ጥፋተኝነቱን ካመነ ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቱ በተከሳሽ የእምነት ቃል ላይ ብቻ ተመሥርቶ ውሣኔ መስጠት ፍትሕ ያዛባል ብሎ ካመነ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ለማረጋገጥ የሚያስፈልገውን ማስረጃ፣ ተከሳሽም የመከላከያ ማስረጃውን እንዲያቀርቡ ለማዘዝ ይችላል፡፡ በወንጀል ሕግ የተደነገጉት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው ፍርድ ቤቱ የተከሳሹን ጥፋት ማመን ከግንዛቤ በማስገባት የቅጣት ቅነሣ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ከላይ የተጠቀሱ ሁኔታዎች በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል መልኩ በመስኩ በሚወጡ ወይም የሚሻሻሉ ሕጎች ውስጥ መደንገግ ይኖርባቸዋል፡፡

### 4.5.5 ክስን ስለማንሣት ወይም ክርክርን ስለማቋረጥ

ዐቃቤ ሕግ የመሠረተውን የወንጀል ክስ ክርክር መቀጠል የሕዝብን እና የመንግሥትን ጥቅም አያስጠብቅም ብሎ ባመነ ጊዜ ለፍርድ ቤቱ በማስታወቅ ክሱን ማቋረጥ ይችላል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ያቋረጠበትን ምክንያት በጽሑፍ ዘርዝሮ ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ወይም ለበላይ ዐቃቤ ሕግ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ በዐቃቤ ሕግ ውሣኔ የተነሣ ክስ በጊዜ ገደቡ እና በሕጋዊ ምክንያት መቀጠል የማይቻል ካልሆነ በስተቀር ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የተቋረጠው የክስ ሂደት እንደገና መቀጠል የሚችል ስለመሆኑ አግባብነት ባላቸው ሕጎች ይደነገጋል፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com

## 4.6 ከመደበኛ የፍርድ ሂደት ውጭ ያሉ አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች

### 4.6.1 ጠቅላላ

የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱን ውጤታማ፣ ቀልጣፋ እና ተደራሽ ለማድረግ እንዲቻል በፖሊሲና በሕግ ማዕቀፍ ውስጥ የአማራጭ መፍትሔ እርምጃ መርሆዎች ሊካተቱ ይገባል፡፡ ከምርመራ ጀምሮ በየትኛውም የፍርድ ሂደት ላይ ያለን የወንጀል ጉዳይ በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ ጠያቂነት ወይም በፍርድ ቤቱ አነሣሽነት በመታየት ላይ ያለው ጉዳይ በአማራጭ ዘዴ እንዲፈታ ሊደረግ ይችላል፡፡

ተጠርጣሪን ጥፋተኛ ሊያሰኝ የሚችል ማስረጃ ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ በተጠርጣሪና በግል ተበዳይ መካከል የተፈጠረው የወንጀል ምክንያት በፍትሐብሔር እና በሌሎች ከፍርድ ሂደት ውጭ ባሉ አማራጭ ዘዴዎች ዘላቂ መፍትሔ ያገኛል ብሎ ካመነ ክስ ላይመሰርት ይችላል፡፡

አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎችን በተመለከተ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ የተጠቀሱትን ሥርዓቶችና አሠራሮችን በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ በማካተት የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት በሚያስችል አኳኋን አግባብነት ያላቸው ሕጐችና ኘሮግራሞች መሻሻል ወይም መቀረጽ ይኖርባቸዋል፡፡

### 4.6.2 አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች

#### 4.6.2.1 መርህ

የአማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች ተግባራዊነት በሚከተሉት መርሆዎች ላይ ሊመሠረቱ እና እነዚህንም እርምጃዎች ለማስፈፀም በሚወጡ ወይም በሚሻሻሉ ሕጎች ውስጥ ሊካተቱ ይገባል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) የአማራጭ መፍትሔ ዓላማ አንድን የወንጀል ተጠርጣሪ በፍርድ ቤት ከመክሰስ ይልቅ በራሱ ፈቃድ ኃላፊነት እንዲወስድ በማድረግ አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ይህም የግል ተበዳዩንና ወንጀል አድራጊውን በማስታረቅ እንዲሁም ተጠርጣሪው ለግል ተበዳዩ ካሣ እንዲከፍል በማድረግ ሊከናወን ይችላል፡፡

(ለ) አማራጭ መፍትሔ ተግባራዊ የሚደረገው የወንጀሉን ዓይነት፣ የተጠርጣሪውን ባሕርይ እና የወንጀሉ አፈፃፀም ከባቢያዊ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት ሲሆን ከመደበኛ የፍርድ ሂደት ይልቅ በአማራጭ መፍትሔ እርምጃዎች የሕዝብ ጥቅም የሚከበር መሆኑ ሲታመን ነው፡፡ በአጠቃላይ አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች ተግባራዊ የሚሆኑት በወጣት ወንጀል

አድራጊዎች፣ ደጋጋሚ ባልሆኑ ተጠርጣሪዎች ወይም በቀላል እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች በፈፀሙ ሰዎች ላይ ይሆናል፡፡

### 4.6.2.2 የአማራጭ መፍትሔ እርምጃ መስፈርቶች

አማራጭ የመፍትሔ እርምጃ ተግባራዊ የሚደረገው የሚከተሉት መስፈርቶች በአንድነት ሲሟሉ ብቻ ይሆናል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) ተጠርጣሪውን ወይም ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ ማስረጃ መኖሩ ሲረጋገጥ፤

(ለ) ጉዳዩ በአማራጭ የመፍትሔ እርምጃ መታየቱ የሕዝብን ጥቅምና የተጎጂውን መብቶች በተሻለ የሚያስጠብቅ ከሆነ፤

(ሐ) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ሁሉም የወንጀሉን መሠረታዊ ነገሮች በሙሉ ፈቃዱ መፈፀሙን ሲያምን እና ድርጊቱን በመፈፀሙም ከልቡ መፀፀቱን በጽሑፍ ሲገልፅ፤

(መ) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ የወንጀሉን መሠረታዊ ነገሮች መፈፀሙን ከማመኑ በፊት በቂ የሕግ ምክር ያገኘ ከሆነ፤ እና

(ሠ) ተጠርጣሪው ጉዳዩን ወደ አማራጭ የመፍትሔ እርምጃ እንዳይመራ ያለመስማማት መብት ያለው መሆኑ የተነገረው ከሆነ፤ ነው፡፡

ከላይ ከተመለከተው በተጨማሪ አማራጭ የመፍትሔ እርምጃ ተግባራዊ የማድረግ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት ተጠርጣሪው ስለሚቀርብበት ክስና የማስረጃ ዝርዝር እንዲያገኝ መደረግ አለበት፡፡

### 4.6.2.3 አማራጭ የመፍትሔ እርምጃ ተፈፃሚ ስለሚሆንበት ሁኔታዎች

ከላይ በተራ ቁጥር 4.6.2.2 ሥር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አማራጭ የመፍትሔ እርምጃ ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩና በሌሎችም ተመሳሳይ ሁኔታዎች በአንዱ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ወጣት ወንጀል አድራጊ ወይም ሴት ወይም አካል ጉዳተኛ ወይም አረጋዊ ከሆነ፤

(ለ) ጉዳዩ በመደበኛ የፍርድ ሂደት ቢሰማ በተጎጅዎችና በምስክሮች ላይ ከፍተኛ አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ፤

(ሐ) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ወንጀሉን በሚፈፅምበት ወይም በክስ መሰማት ጊዜ ከፍተኛ አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ህመም ውስጥ ከሆነ፤ ወይም

(መ) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በተጎጅው ላይ ለደረሰው በደል ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ለመክፈል ወይም የደረሰውን ጥፋት ለማስተካከል ዝግጁ፤ ከሆነ የሚሉ ናቸው፡፡

በዚህ ተራ ቁጥር ሥር የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ውሳኔ ሲወስን እንደነገሩ ሁኔታ በጉዳዩ ላይ እውቀት ያለው ባለሙያ፣ በወንጀሉ የተጎዳ ሰው ወይም ሌሎች ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው አካላት ሊያማክር ይገባል፡፡

### 4.6.2.4 ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ስለሚዘረጋው ሥርዓት

ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በሚከተሉት ዋና ዋና ሁኔታዎች ላይ በመመሥረት ከመደበኛው የፍርድ ሂደት ወደ አማራጭ መፍትሔ እርምጃ ተመርተው መፍትሔ ማግኘት የሚችሉ ወይም የማይችሉ የወንጀል ጉዳዮች፣ ተጠርጣሪዎች ወይም ተከሳሾች የሚለዩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

(ሀ) የወንጀሉ ክብደት፣ ዓይነትና ባሕርይ፤

(ለ) ወንጀሉ የተፈፀመበት ሁኔታና ዘዴ፤

(ሐ) የተጠርጣሪው ወይም የተከሳሹ ባሕርይና የወንጀል ሪከርድ፤

(መ) የተጠርጣሪው ወይም የተከሳሹ ዕድሜና ማኀበራዊ ሁኔታ፤

(ሠ) በተጎጅው ላይ የደረሰው የጉዳት መጠንና ዓይነት፤

(ረ) የተጎጅው ፆታ፣ ዕድሜ እና ሌሎች ማኀበራዊ ሁኔታዎች፤

(ሰ) ሌሎችም አግባብነት ያላቸው ተመሳሳይ ሁኔታዎች፤

### 4.6.2.5 በዐቃቤ ሕግ ስለሚወሰን አማራጭ የመፍትሔ እርምጃ

በዚህ ፖሊሲ መሠረት የጥፋተኝነት ድርድር የሚካሔድበት ሁኔታ ቢኖርም አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች ዐቃቤ ሕግ ተግባራዊ የሚያደርገው ተፈፀመ ከተባለው የወንጀል ድርጊት እና ከተጠርጣሪው ባሕርይ አንፃር ሲመዘን በፍርድ ቤት ክስ ከመመሥረት እና መደበኛውን ቅጣት ከመፈፀም ይልቅ ሌሎች አማራጭ እርምጃዎችን መውሰድ ተጠርጣሪው ከወንጀል ባሕርይው እንዲላቀቅ እና በኀብረተሰቡ ውስጥ በሰላም እንዲኖር ያስችላል ተብሎ ሲያምን ብቻ ነው፡፡ ዐቃቤ ሕግ የተጠርጣሪውን አደገኝነት እና የደጋጋሚነት ሁኔታ፣ የወንጀሉ በተደራጁ ቡድኖች፣ በጦር መሣሪያ ወይም በኃይል የተፈፀመ አለመሆኑ እንዲሁም ድርጊቱ ከጾታ ጥቃት ጋር ተያያዥነት የሌለው መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከተሉትን አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) ተጠርጣሪው በራሱ ወይም በመንግሥት ወጭ ሕክምና እንዲከታተል፣ ሙያዊ ሥልጠና እንዲወስድ የቀለም፣ የሙያ ወይም የግብረገብ ትምህርት በሚሰጥበት ተቋም በመግባት ትምህርቱን እንዲከታተል፤

(ለ) የማስታረቅ ሥራ የሚሠሩ የመንግሥት ወይም የግል ተቋማትን በመጠቀም ከተበዳይ ጋር እንዲታረቅ እና ካሣ እንዲከፍል ማድረግ፤

(ሐ) ለኅብረተሰቡ የተወሰነበትን ማኅበራዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፤

(መ) ለተወሰነ ጊዜ በተወሰነ ቦታ ብቻ እንዲቆይ ማድረግ እና ሌሎችም ሊሆኑ ይችላሉ።

## 4.7 በጠበቃ ስለመወከልና የተከላካይ ጠበቆችን ሙያዊ ብቃትና ሥነ-ምግባር ስለማጎልበት

### 4.7.1 በጠበቃ ስለመወከል

የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱን ውጤታማነት፣ ፍትሐዊነት፣ ቀልጣፋነት፣ ተደራሽነትና ሚዛናዊነት ለማረጋገጥ በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች ራሳቸውን ከቀረበባቸው ክስ ለመከላከል በሚያስችላቸው ደረጃ በጠበቃ መወከላቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት በዋናነት የመርማሪ አካል፣ የዐቃቤ ሕግ እና የፍርድ ቤት ይሆናል። በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች ወይም ጠበቃቸው በማንኛውም የፍርድ ሂደት ከዐቃቤ ሕግ በዕኩል ደረጃ ጉዳያቸውን የማሰማት መብታቸው በሚረጋገጥበት መልኩ የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ የሁሉም የፍትሕ አካላት ኃላፊነት ሲሆን ጉዳያቸው የሚታይበት ፍርድ ቤት ወይም ችሎት ይህንን መብት ከማስከበር አንፃር የጐላ ሚና ሊጫወቱ ይገባል።

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው በመስኩ የሚወጡ ወይም የሚሻሻሉ ሕጎች የሚከሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች በሚያካትት መልኩ መቀረጽ ይኖርባቸዋል። እነዚህም፡-

(ሀ) ማንኛውም በወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ የተያዘ ወይም የታሰረ ሰው ከተያዘበት ወይም ከታሰረበት ጊዜ ጀምሮ በማንኛውም የፍርድ ሂደት ወቅት እሱ ከመረጠው አማካሪ ምክርና ድጋፍ የማግኘት ወይም ከተመሠረተበት ክስ ራሱን ለመከላከል በመረጠው ጠበቃ የመወከል መብቱ የተጠበቀለት መሆኑን፤

(ለ) በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች ከተመሠረተባቸው ክስ ራሳቸውን ለመከላከል ጠበቃ ለማቆም የገንዘብ አቅም የሌላቸው መሆኑ ከተረጋገጠ እና በዚህም ምክንያት ፍትሕ የሚዛባ መሆኑ ከታመነ ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑ፤

(ሐ) ማንኛውም የሕግ አስከባሪ አካል ወንጀል ፈፅመዋል በሚል ምክንያት ሰዎችን በሚይዝበት ወይም በሚያስርበት ጊዜ ተጠርጣሪዎቹ ጠበቃ የማግኘት መብት እንዳላቸው በሚገባቸው ቋንቋ የማስረዳት እና ጠበቃ በቀላሉ ለማግኘት እንዲችሉ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ግዴታ እንዳለበት፤

(መ) በከባድ የወንጀል ድርጊት ወይም በሰብዓዊ መብት መጣስ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ካሣ ለማግኘት በፍርድ ቤት በሚያደርጉት ክርክር ጠበቃ ወክለው ለመከራከር አቅም የሌላቸው መሆኑ ከተረጋገጠና በዚህም የፍትሕ መጓደል የሚከተል መሆኑ ከታመነ መንግሥት ጠበቃ የሚያቆምላቸው መሆኑን ያካተቱ ናቸው፡፡

በዚህ ተራ ቁጥር ሥር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠበቃ ለማቆም አቅም የሌላቸውን ተጠርጣሪዎች ወይም ተከሳሾች ጠበቃ እንዲያገኙ ለማስቻል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሕግ ባለሙያዎች፣ ጠበቆች ወይም የጠበቆች ማኅበር ነፃ የሕግ አገልግሎት የሚሰጡበትን ሥርዓት የመዘርጋት ኃላፊነት አለበት፡፡

#### 4.7.2 <u>የተከላካይ ጠበቆች ሙያን ስለማጎልበት</u>

የተከሳሾችን መብት ለማስከበር እና በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ተከሳሾች በበቂ ሁኔታ መወከላቸውን ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ነፃና ገለልተኛ የሆነ የተከላካይ ጠበቆች ተቋም ሊኖር ይገባል፡፡ የሕግ ሙያን ለማጠናከር ሲባል ከሕግ ትምህርት ቤትና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችሉ አሠራሮች ሊፈጠሩ ይገባል፡፡

### 4.8 <u>የይግባኝ ሥርዓትን ስለማጠናከርና የካሣ ክፍያ</u>

#### 4.8.1 <u>የይግባኝ ሥርዓትን ስለማጠናከር</u>

በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ያለውን የይግባኝ ሥርዓት ለማጠናከር የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የአሠራር ሥርዓቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት በሚከተሉት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ይመሠረታል፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com

#### 4.8.1.1 ስለይግባኝ

ማንኛውም ሰው በወንጀል በተከሰሰበት ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ወይም ፍርድ የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ስህተት አለው ብሎ ካመነ ቅሬታውን በሕግ ተለይቶ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት በጽሑፍ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ዐቃቤ ሕግ ፍርድ ቤት በሚሰጠው ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ይግባኝ የሚጠይቀው የተሰጠው ትዕዛዝ ወይም ውሣኔ የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ስህተት ካለው እና በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ባይቀርብበት የሕዝብ ጥቅም የሚጐዳ መሆኑን ካመነ ብቻ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱ ሁኔታዎች በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ በመስኩ በሚወጡ ወይም በሚሻሻሉ ሕጎች ውስጥ መደንገግ ይኖርባቸዋል፡፡

#### 4.8.1.2 ስለሰበር

ዐቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሽ ተካፋይ በሆኑበት የወንጀል ክርክር ላይ ፍርድ ቤት የሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለው ብሎ ካመነ ጉዳዩን በሰበር ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

#### 4.8.1.3 የመጨረሻ ውሣኔን እንደገና ስለማየት

ፍርድ ቤት በሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ከውሣኔው በኂላ ጥፋተኛ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ከተገኘ በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሹ አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ በሰጠው ፍርድ ቤት እንደገና ታይቶ ተከሳሹ ከወንጀል ነፃ ሊደረግ የሚችልበት ሥርዓት በተዛማጅ ሕጎች ውስጥ በግልጽ እንዲሰፍር ይደረጋል፡፡

### 4.8.2 የካሣ ክፍያ

በፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሣኔ ጥፋተኛ ተብለው የታሠሩ ወይም በሞት የተቀጡ ወይም በገንዘብ መቀጮ የተቀጡ ሰዎች የተቀጡበትን የወንጀል ድርጊት አለመፈፀማቸው ወይም ጥፋተኛ አለመሆናቸው የመጨረሻ ውሳኔን እንደገና በማየት ሥነ ሥርዓት መሠረት በፍርድ ቤት ከተረጋገጠ ቅጣቱን ባስከተለው ውሣኔ ምክንያት ለደረሰባቸው የሞራልና የንብረት ጉዳት ለተጎጅው ወይም ለወራሾቹ ወይም ለትዳር ጓዳኛው ከደረሰበባቸው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ካሣ ከመንግሥት የማግኘት መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ አግባብነት ባላቸው ሕጎች ውስጥ ይደነገጋል፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com

## 4.9 የኮምፒውተርና የኢንተርኔት ወንጀሎች

የኮምፒውተርና የኢንተርኔት አገልግሎት የሰው ልጅ የግንኙነትና የመረጃ ልውውጥ ዘዴዎች በቦታና በጊዜ ሳይገደቡ እጅግ በጣም ቀላል፣ ፈጣንና ምቹ በሆነ መልኩ እንዲያከናውኑ በማድረግ ንግድ፣ ሳይንስ፣ ትምህርት፣ ባህል እና ቋንቋ እንዲሁም ሌሎች የሰው ልጅ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብቶች እንዲያድጉና እንዲበለፅጉ በማድረግ ለአጠቃላይ የሰው ልጆች ኑሮ መሻሻል እያበረከተ ያለው አስተዋፅኦ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ይሁንና በቀላል ወጭና ድካም፣ አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ ዝግጅት በማድረግ በየትኛውም ጊዜና የዓለማችን ክፍል በመሆን የኮምፒውተር ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት የሚጠቀም ተቋም ወይም ግለሰብ ላይ ከባድ ጉዳት ሊያደርሱ እና የሀገርን ብሔራዊ ደህንነት ለከፍተኛ አደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉትን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ነባርና አዳዲስ ወንጀሎችን ለመፈፀም ፍላጎት ያላቸው ሰዎችን ለማገልገል የሚችል አደገኛ መሣሪያም ሊሆን ይችላል፡፡

በመሆኑም የኮምፒውተርና የኢንተርኔት አገልግሎትን በተመለከተ በአንድ በኩል ሕዝብና መንግሥት ከአገልግሎቱ ማግኘት የሚችሉትን ጥቅሞች በተቻለ መጠን ያለምንም እንከን ማግኘት የሚችሉበትን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ወንጀለኞች አገልግሎቱን እንደመሣሪያ በመጠቀም በሕዝቡ ሰላምና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ አስቀድሞ መከላከል የሚቻልበት እና ጉዳቱን አድርሰው በተገኙት ላይ ተመጣጣኝ ቅጣት ሊያገኙ የሚችሉበት ከአለማችን ተጨባጭ እውነታ ጋር አብሮ መራመድ የሚችል ዘመናዊና ውጤታማ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት መገንባት የግድ ይላል፡፡

ስለዚህ ከኮምፒውተርና ከኢንተርኔት ወንጀሎች አኳያ የታሰበውን ዓይነት የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ለመገንባት የሚከተሉት ዋና ዋና እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) ሀገር አቀፍ የወንጀል መከላከል ስትራቴጅ ሲቀረጽ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚመነጩትን የኮምፒውተርና የኢንተርኔት ወንጀሎች መንስዔዎችና መከላከያ ዘዴዎች በግልጽና በዝርዝር ማመላከት ይኖርበታል፡፡

(ለ) ኮምፒውተር ወይም ኢንተርኔት የሚጠቀሙ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ከሥራቸው ጋር በተያያዘ የሚይዟቸው ማስረጃዎችና ዳታዎች ላይ ወንጀል እንዳይፈፀምባቸው ለመከላከል፣ ከተፈፀመባቸውም ፈፃሚውን አካል በቀላሉ ለመለየት በሚያስችል መልኩ እንዲደራጁ የሚያስገድዷቸው ተገቢ ሕጎች ተቀርፀው በሥራ ላይ መዋል አለባቸው፡፡

(ሐ) የኮምፒውተርና የኢንተርኔት ወንጀሎች አለም አቀፍ ባሕርይ ያላቸው በአብዛኛውም የሚፈፀሙት ከውጭ ሀገር በሚገኙ ሰዎች ሆኖ በረቀቀና በተወሳሰበ አኳኋን ከፍተኛ ጉዳት

ለማድረስ የሚፈፀሙና በተለመደውና በመደበኛው የወንጀል ምርመራና የክስ አሠራር ተጠርጣሪዎችን ለፍርድ ቤት አቅርቦ ማስቀጣት አስቸጋሪ መሆኑንና ሌሎችም የወንጀሎቹን ልዩ ባሕርያት ባገናዘበ መልኩ የወንጀልና በመስኩ የሚወጡ ሌሎች ሕጎች መሻሻልና መቀረፅ ይኖርባቸዋል፡፡

(መ) የኮምፒውተርና የኢንተርኔት ወንጀሎችን በተመለከተ የሚኖረን የዓለም አቀፍ ትብብር የሚመራበት ግልጽና ዝርዝር ሥርዓት በሚመለከታቸው አካላት ተቀርፆ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

(ሠ) እነዚህን ወንጀሎች ለመከላከል፣ ለመመርመር እና ለመክሰስ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችላቸውን አቅም የመገንባት፣ ምቹ የአደረጃጀት እና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

## 4.10 <u>የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱን አፈፃፀም ስለመከታተል</u>

የፍትሕ አካላት ከወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ጋር የተያያዙ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የመተንተን እና የማሰራጨት ግዴታ እንዲሁም ለሥራቸው ቅልጥፍና፣ ውጤታማነት እንዲሁም ግልጽነት ተጠያቂነት አስፈላጊ የሆነ የመረጃ ቴክኖሎጂ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር መረጃ ማዕከል እንደአስፈላጊነቱ በክልል እና በፌዴራል ደረጃ የሚመሠረት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሀገር አቀፍ የወንጀል መረጃ ማዕከል በፍትሕ ሚኒስቴር ሥር ይቋቋማል፡፡ ሁሉም የፍትሕ አካላት ቁልፍ የሆኑ የአፈፃፀም መለኪያዎችን በሥራ ላይ እንዲያውሉ የሚያስችሉ እና ለክትትል የሚረዱ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

## 4.11 <u>በፌዴራልና በክልል የፍትሕ አካላት መካከል ስለሚኖር የሥራ ትብብር እና ግንኙነት</u>

የፌዴራልና የየክልሉ የፍትሕ ተቋማት የፍትሕ አስተዳደሩን አስመልክቶ የሚዘጋጁ ዕቅዶችን በጋራ የማቀድና የመገምገም እንዲሁም እንደመሠረተ ልማት ያሉ ሌሎች የጋራ ሥራዎችን አብሮ የመሥራት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወንጀልን በመከላከል፤ የወንጀል ሕጎችንና የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲን በማስፈፀምና በማፈፀም ዙሪያ የእነዚህ ተቋማት የጐንዮሽና የቀጥታ የግንኙነት ሥርዓት በመስኩ በሚወጡ ሕጎች ይወሰናል፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com

# ክፍል አምስት

# የወንጀል ቅጣት አፈፃፀም ፍትሐዊነትና ውጤታማነትን ስለማሻሻል

## 5.1 የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ይዘት

የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ዜጎች ስለቅጣት ዓላማ እንዲሁም ቅጣቱ በእያንዳንዱ የወንጀል ጉዳይ እንዴት ተግባራዊ እንደሚደረግ ግልጽ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከማድረጉም በተጨማሪ ቅጣቱ በማን እንደሚወሰን፣ የሚወሰንበት የጊዜ ገደብ፣ ቅጣቱን ለመወሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎች እና የቅጣት ውሣኔ በሚሰጥበት ጊዜ ሊከበሩ የሚገባቸው መርሆዎችን የሚያመላክት ነው፡፡ የቅጣት ውሣኔ በሚሰጥበት ጊዜ ከወንጀሉና ከወንጀለኛው ባሕርይ ጋር የሚገናኙ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህም ረገድ በቅጣት አወሣሠን መመሪያ ውስጥ ቅጣትን ሊያከብዱ ወይም ሊያቀሉ የሚችሉ ምክንያቶች በግልጽ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ዐቃቤ ሕግ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ ቅጣትን የሚያከብዱ ምክንያቶች መኖራቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት በሚዘጋጀው የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ውስጥ በግልጽና በዝርዝር መካተት ይኖርበታል፡፡

የቅጣት አወሣሠን መመሪያ የወንጀል አድራጊውን ባሕርይ፣ የተፈፀመውን ወንጀል ሁኔታ ከግምት በማስገባት ሊወሰን የሚችለውን የቅጣት ዓይነት እና ወንጀለኛውን በመቅጣት ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም መግለፅ ይኖርበታል፡፡ ይህም የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡፡

(ሀ) ወንጀል አድራጊዎችንና የወንጀል ባሕርያቶችን ማውገዝ፤

(ለ) ወንጀል ፈፃሚዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎችም ማስተማሪያ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ሐ) ወንጀል ፈፃሚዎችን አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ከኅብረተሰቡ በእሥር እንዲገለሉ ማድረግ፤

(መ) የወንጀል ባሕርያትን በመንቀፍ ተኃድሶ እንዲያደርጉ በማድረግ እና በማስተማር ወደፊት ለሚፈፅሟቸው ድርጊቶች የኃላፊነት ስሜት እንዲኖራቸው ማድረግ፤

(ሠ) በወንጀል ድርጊት ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ግለሰቦች ካሣ እንዲከፈል ወይም ኅብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ የሚሉ ናቸው፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com

### 5.2 የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ስለማዘጋጀት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር የወንጀል ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ቅጣቶች የሚመሠረቱባቸው መርሆዎችንና መስፈርቶችን የያዘ በፍትሐዊነት፣ በግልጽነት እና በውሳኔ ተገማችነት ላይ የተመሠረተ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

### 5.3 ቅጣትንና ሌሎች እርምጃዎችን ስለማስፈፀም

ቅጣትንና ሌሎች እርምጃዎችን የማስፈፀም ዓላማ በወንጀል ጉዳዮች ላይ የሚወሰዱ የተለያዩ ውሣኔዎችን ፍትሐዊ፣ ግልጽና ተገማች በሆነ አሠራር በማስፈፀም ቅጣቱ የሚፈፀምበት ሰው ታርሞ አምራች ዜጋ እንዲሆንና ከኅብረተሰቡ ጋር ተቀላቅሎ ሰላማዊ ኑሮ እንዲኖር በማስቻል የመንግሥት፣ የሕዝቦች እና የነዋሪዎች ሰላም፣ ደህንነት፣ መብትና ጥቅም እንዲጠበቅና እንዲረጋገጥ ማስቻል ነው፡፡ በመሆኑም የሚፈፀሙ ቅጣቶችና ሌሎች የእርምት እርምጃዎች ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉት አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደርጋሉ፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ታራሚዎች ሰብዓዊ ክብራቸው በተጠበቀ አያያዝ ታርመውና አምራች ዜጋ ሆነው ከኅብረተሰቡ ጋር የሚቀላቀሉበትን ስትራቴጂዎችና ኘሮግራሞች የሚመለከታቸውን የመንግሥት አካላት፣ ማኅበራትንና በጎ አድራጎት ድርጅቶችን፣ የግሉን ሴክተር እና ማኅበረሰቡን በማሣተፍ የመንደፍና የመተግበር ኃላፊነት አለበት፡፡

(ለ) የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የታራሚዎችን ቁጥር ለመቀነስ እንዲቻል ከእሥር ውጭ ያሉ ሌሎች አማራጮችን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሏቸውን መንገዶች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የማጥናትና በጥናት የተገኙ ውጤቶችንም ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

(ሐ) ማረሚያ ቤቶች ታራሚዎችን በተፈለገው መልኩ ለማረም የሚያስችላቸውን ተቋማዊ አቅም መገንባት ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም እንደ የታራሚዎች አያያዝ፣ የምርምርና ጥናት ዘዴዎች፣ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ ታራሚዎችን ለማረም የሚውሉ ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅቶችና በመሳሰሉ ጉዳዮች ዙሪያ በአግባቡ የተጠና ኘሮግራም በማውጣት ተቋማዊ አቅማቸውን ማሳደግ ይኖርባቸዋል፡፡

(መ) በታራሚዎች ላይ የተላለፉ የቅጣት ወይም አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች የተፈለገውን ውጤት ማስገኘታቸውን በማረሚያ ቤቶች፣ በፍትሕ ሚኒስቴር፣ በፍርድ ቤቶችና ይህንን ተግባር ለማከናወን በሚቋቋሙ አካላት የጋራ ኘሮግራም ክትትል ይደረግበታል፡፡

(ሠ) ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው በሚያሳዩት የባሕርይ ለውጥ፣ የአምራችነት ጥረት፣ መልካም ሥነ ምግባርና በመሳሰሉት ሌሎች ሥራዎች የአመክሮና የይቅርታ ተጠቃሚ የሚሆኑበት በእኩልነትና በግልጽነት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

## ክፍል ስድስት

## በጋራ መብቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን የወንጀል ድርጊት ስለማድረግ እና ለሌሎች ለወንጀል ጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ስለሚደረግ የተለየ አያያዝ

### 6.1 በጋራ መብቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ወይም ጉዳቶችን የወንጀል ድርጊት ስለማድረግ

በሕገ መንግሥቱ ዕውቅና ካገኙትና ከፍተኛ ጥበቃ ከተደረገላቸው መብቶች መካከል የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች መብት በዋናነት ከሚጠቀሱት አንዱ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሕገ-መንግሥቱ ለኃይማኖትና ለዕምነት እንዲሁም ለቋንቋና ለሌሎች የማንነት መገለጫ ለሆኑ መብቶች ዕውቅና የሚሰጥና ጥበቃ የሚያደርግ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በተጨማሪም ማንም ሰው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ፣ በሕዝቡ፣ በዘሩ፣ በቋንቋው፣ በኃይማኖቱ፣ በማኅበራዊ አመጣጡ እና በመሳሰሉት ምክንያቶች ምንም ልዩነት ሳይደረግበት በሕግ ፊት እኩል እንደሆነ እና በእኩልነትም ተጨባጭ የሕግ ዋስትና እንደሚያገኝ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ከዚህም በመነሳት ማንኛውም ሕዝብ ወይም ማኅበረሰብ እንዲሁም የሕዝቡ ወይም የማኅበረሰቡ አባል በሕገ መንግሥቱ ዕውቅና እና ጥበቃ ካገኙ መብቶቹ ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚ እንዲሆንና መብቶቹ መከበራቸውን ለማረጋገጥ እንዲችል በመንግሥት ሊከናወኑ የሚገቡ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች መኖራቸው የሚታወቅ ነው፡፡ በመንግሥት መከናወን ከሚገቡ ከእነዚህ ሥራዎች መካከል በእነዚህ መብቶች ወይም ለአንድ ሕዝብ ወይም ማኅበረሰብ ከሚኖረው ጥላቻ በመነሳት በዚህ ሕዝብ ወይም ማኅበረሰብ አባላት ላይ የሚፈፀሙ የተለያዩ ጥቃቶች ወይም ጉዳቶች በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ የወንጀል ድርጊቶች ሆነው የድርጊቱ ፈፃሚዎች መቀጣት መቻላቸውን የማረጋገጥ ሥራ አንዱና መሠረታዊ ነው፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com

በማንኛውም ሕዝብ ወይም ማኅበረሰብ መብቶች ወይም ለአንድ ሕዝብ ወይም ማኅበረሰብ ከሚኖረው ጥላቻ በመነሳት በዚህ ሕዝብ ወይም ማኅበረሰብ አባላት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች ወይም ወንጀሎች ከማንኛውም የወንጀል ድርጊት የበለጠ ሊተካ ወይም ሊካስ የማይችል ጉዳቶችን በመንግሥት፣ በሕዝብ ወይም ማኅበረሰብ እንዲሁም ግለሰቦችና ነዋሪዎች ላይ የሚያደርሱ መሆናቸው የሚታወቅ ነው፡፡

በመሆኑም የወንጀል ሕጉን ጨምሮ ተዛማጅ በሆኑ ሕጎችና በሌሎች የአሠራር ሥርዓቶች ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች በዝርዝር መካተት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ወይም የማንኛውም የኃይማኖት፣ የቋንቋ ወይም ተለይተው የሚታወቁ የማንኛውም አናሳ ማኅበረሰብ መልካም ስም፣ ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ እምነት ወይም ማንኛውም የማንነት መገለጫ የሆነው ዕሴት ለማጥፋት፣ ለማንቋሸሽ፣ የማይጠቅም ወይም ከሌላ ያነሰ አድርጎ ለማቅረብ፣ እንዲናቁ ወይም እንዲጠሉ ለማድረግ በማንነታቸውና በራሳቸው እንዲያፍሩ ወይም እንዳያምኑ ለማድረግና ሌሎች በተመሳሳይ የሚፈፀሙ ድርጊቶች የወንጀል ድርጊት መሆናቸውን፤

(ለ) ለአንድ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ፣ ወይም ማንኛውም የኃይማኖት፣ የቋንቋ ወይም ተለይቶ ለሚታወቅ ማንኛውም አናሳ ማኅበረሰብ ከሚኖረው ጥላቻ በመነሳት በዚሁ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ፣ ወይም ማኅበረሰብ አባል ላይ የሚፈፀም ወንጀል ከተፈፀመው ወንጀል በተጨማሪ ሌላ የወንጀል ድርጊት እንደሚሆንና ይህም የጥላቻ ወንጀል በመሆኑ የራሱ የወንጀል ቅጣት ያለው እንደሚሆን፤ እና

(ሐ) በዚህ ቁጥር በፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" ሥር የተመለከቱትን ድርጊቶች የፈፀመ ማንኛውም ሰው በሚወሰንበት የወንጀል ቅጣት በተጨማሪ በፍትሐብሔር ኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል መሆኑን፤ የሚሉ ናቸው፡፡

### 6.2 <u>በወንጀል ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች መብት ስለማስከበር</u>

በወንጀል ድርጊት ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች መብት በአግባቡ ማስከበር እንዲቻል የተፈፀመው የወንጀል ዓይነት ወይም የተጎጂውን ግላዊ ሁኔታ መሠረት ያደረገ እና ለልዩ ፍላጎቶቻቸውም ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ላይ ያተኮረ አሠራር በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ ሕፃናትን ጨምሮ ሌሎች በሁኔታቸው በወንጀል ድርጊት ለሚደርስ ጉዳት ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች ተገቢውን ጥበቃ እና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችሉ ልዩ የጥንቃቄ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡ በወንጀል ድርጊት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ለደረሰው ጉዳት በፍርድ ቤት

http://ethcriminalawnetwork.com

ወይም በሌሎች አማራጭ ዘዴዎች የካሣ ጥያቄ በማቅረብ ተገቢውን ካሣ በአፋጣኝ እንዲያገኙ ማድረግ የሚያስችል አመቺ የሆነ የአሠራር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ የወንጀል ተጐጂዎች በተፈፀመባቸው የወንጀል ድርጊት ሣቢያ ከደረሰባቸው ሥነ-ልቦናዊ ቀውስ እና ካጋጠማቸው ሌሎችም ተያያዥ ችግሮች በአግባቡ እንዲላቀቁ ተገቢ የሆነ ድጋፍ እና የምክር አገልግሎት የሚያገኙበት ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

### 6.2.1 <u>የተጐጂዎች በወንጀል ምርመራ፣ ክስ እና የፍርድ ሂደት ተሳትፎ የማድረግና መረጃ የማግኘት መብት</u>

በወንጀል ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው በጉዳዩ ላይ በሚደረገው የምርመራ፣ የክስ አቀራረብ እና የፍርድ ሂደት ውስጥ ተሣትፎ የማድረግ እንዲሁም ጉዳዩ የደረሰበትን ደረጃ በቅርብ የመከታተል እና ስለሚሰጡት ውሣኔዎች ተገቢውን መረጃ የማግኘት እንዲሁም የደረሰበትን የጉዳት መጠን፣ ዕድሜውን፣ ችሎታውን እና የማኀበራዊ ኑሮ መሠረቱን ባገናዘበ መልኩ በክብርና በርህራሄ የመያዝ መብት አለው፡፡

በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ በወንጀል ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች መብትና ፍላጐት ከማስከበር አኳያ ውጤታማ ሥራ መሥራት እንዲቻል የሚከተሉት መሠረታዊ ነገሮች እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) የወንጀል እና የሥነ ሥርዓት ሕጐች የሁሉንም የወንጀል ተጐጂዎች መብት ማስከበር በሚያስችል መልኩ ይሻሻላሉ፡፡

(ለ) በወንጀል ጉዳት የደረሰባቸውን ሕፃናት መብት እና ፍላጐት ማስጠበቅ የሚያስችሉ የሕግ ድንጋጌዎች ይቀረፃሉ፡፡

(ሐ) በወንጀል ድርጊት የተጠረጠሩና ተጎጅ የሆኑ ሴቶችን እንዲሁም የጾታ ጥቃት ሰለባ ለሆኑ ሰዎች የሚደረገውን የተለየ አያያዝ የሚመለከቱ ግልጽ የሕግ ድንጋጌዎች በሕጎች ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡

(መ) በወንጀል ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የድጋፍ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እና ድርጅቶች ተገቢው የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

(ሠ) ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሕግ አስፈፃሚ እና የፍትሕ አካላት በወንጀል ጉዳት ከደረሰባቸው ሕፃናት ጋር በተያያዘ ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት እና ስለሚወስዷቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

(ረ) በወንጀል ተጐጂ የሆኑ ሰዎች በፍርድ ቤት ቀርበው በሚመሰክሩበት ጊዜ ደኅንነታቸው፣ የግል ምስጢራቸው እና ማንነታቸው እንዲጠበቅ ወይም እንዳይገለፅ ሲባል ለምስክሮች ከሚሰጥ ልዩ ጥበቃ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው አስፈላጊ የሆኑ ጥበቃዎች እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

## 6.3 <u>የሕፃናት ወይም የወጣቶች የወንጀል ፍትሕ መሠረታዊ መርሆዎች</u>

በሀገራችን የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ከሕፃናት ወይም ከወጣቶች ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚወሰኑ እና የሚተገበሩ ውሣኔዎች፣ የሚታወጁ ሕጎች፣ የሚዘጋጁ መመሪያዎች፣ ፕሮግራሞችና ሌሎች ተመሳሳይ የሆኑ የአሠራር ሥርዓቶች፡-

(ሀ) በማንኛውም ሕፃን ወይም ወጣት ላይ በእሱ ወይም በወላጆቹ ወይም በአሳዳሪዎች ዘር፣ ቀለም፣ ፆታ፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ ፖለቲካ ወይም ሌላ አመለካከት፣ ብሔር፣ ኀሣ ወይም ማኅበራዊ ሁኔታ፣ አካል ጉድለት፣ ትውልድ፣ የሥራ እንቅስቃሴ ወይም በሌላ ሁኔታዎች ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩነት የማያደርጉ ወይም አድሎ የማይፈፅሙ፤

(ለ) አስፈላጊ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ ሕፃኑን ወይም የወጣቱን የላቀ ጥቅም የሚያስከብሩ፤ እና

(ሐ) የሕፃኑን ወይም የወጣቱን በሕይወት የመኖርና በመልካም ሁኔታ የማደግ እንዲሁም ተሳትፎ የሚያረጋግጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## 6.4 <u>የወጣት ወንጀል አድራጊዎች አያያዝ</u>

### 6.4.1 <u>ጠቅላላ</u>

በማንኛውም የፍርድ አሰጣጥ ሂደት እና ፍርድ ከተሰጠም በኋላ ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች የሚደረግላቸው አያያዝ ወጣቶቹ ከገቡበት የተሳሳተ መንገድ እንዲወጡ፣ ቀና አስተሳሰብን እንዲያዳብሩ፣ ሠላማዊና ለሕግ ተገዢ የሆነ ዜጋ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ዘዴ የተከተለ መሆን

ይኖርበታል። በዚህ ረገድ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ዋነኛ ዓላማ ወጣቶቹን ማስተማር እና በሂደትም ከቤተሰብና ከማኅበረሰቡ ጋር የተሣካ ውህደት እንዲፈጥሩ ማስቻል መሆን ይኖርበታል።

### 6.4.2 <u>ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች የሚደረግ የሕግ ከለላ</u>

ወጣት ወንጀል አድራጊዎች በሕግ ፊት ሁሉም እኩል ነው በሚል ምክንያት በፍርድ ቤት ቀርበው እንዲመሰክሩ፣ ጥፋታቸውን እንዲያምኑ፣ መስቀለኛ ጥያቄ ሊቀርብባቸው ወይም በዐቃቤ ሕግ ምስክር ሆነው እንዲቀርቡ ሊገደዱ አይገባም።

### 6.4.3 <u>የአማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች ተመራጭነት</u>

ወጣት ወንጀል አድራጊዎችን በተመለከተ የሚወሰዱት እርምጃዎች የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት የማይችሉ ወይም ከተፈፀሙው ወንጀል ልዩ ባሕርይ ወይም የከባድነት ሁኔታ ጋር በተያያዘ መደበኛ ክስ ማቅረብ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ጉዳዩን በአማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች የመፍታት አሠራር ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል።

### 6.4.4 <u>የአማራጭ የመፍትሔ እርምጃች አፈፃፀም</u>

በወጣት ወንጀል አድራጊዎች ላይ አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት የሚሰጣቸው ተቋማት በፌዴራል እና በክልሎች ደረጃ እንዲቋቋሙ ይደረጋል። ተቋማቱ ተግባራዊ የሚደረገውን አማራጭ የመፍትሔ እርምጃ አግባብነት፣ ለወጣቱ የተለየ ሁኔታ ተስማሚ መሆኑን እና ወጣቱ ከፈፀመው የወንጀል ድርጊት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።

በወጣት ወንጀል አድራጊዎች ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች አግባብነት፣ ይዘት፣ ዓይነት እና ዝርዝር አፈፃፀምን አስመልክቶ በመስኩ የሚሻሻሉና የሚቀረፁ ሕጎች፣ መመሪያዎች እና ፕሮግራሞች ሕገ መንግሥታችን ውስጥ የተካተቱን ወይም በሕገ መንግሥቱ መሠረት ዕውቅና ያገኙትን የወጣት ወንጀል አድራጊዎች መብቶችን እና ልዩ ጥበቃዎችን ባገናዘበ መልኩ መሆን ይኖርባቸዋል።

### 6.4.5 <u>ስለልዩ ክፍሎች መቋቋም</u>

የወጣት ወንጀል አድራጊዎችን ጉዳይ የማየት ሥልጣን የሚሰጣቸው ልዩ ችሎቶች በየደረጃው ይቋቋማሉ። በተመሳሳይ መልኩ የወጣት ወንጀል አድራጊዎችን ጉዳይ የመከታተልና የወንጀል ምርመራ የማድረግ ተግባራትን የሚያከናውኑ መርማሪዎች እና ዓቃቤያነ ሕግ ይኖራሉ።

http://ethcriminalawnetwork.com

### 6.5 ለወንጀል ተጋላጭ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ትኩረት ስለመስጠት

የሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ የአረጋዊያንንና ሌሎች ተመሳሳይ አካላትን ለወንጀል ተጋላጭነት እና ከፍተኛ የተጠቂነት ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የወንጀል መከላከል፣ ምርመራ፣ ክስ አቀራረብ እንዲሁም ድጋፍና እርዳታ ተግባራት የሚከናወንበት ልዩ የሆነ ሥርዓት በመርማሪ አካላት፣ በዐቃቤ ሕግ ተቋማት እና ፍርድ ቤቶች ውስጥ እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራል እና የክልል የፍትሕ አካላት ሌሎች በወንጀል መከላከል፣ ምርመራ፣ ክስ አቀራረብ ተግባር ላይ የተሰማሩ እንዲሁም ድጋፍ እና የምክር አገልግሎትን የሚሰጡ የማኅበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲሁም የአለም አቀፍ ድርጅቶች ጥረት ማቀናጀት የሚያስችል የማስተባበር ሥራ ይሠራሉ፡፡ ሁሉም የፍትሕ አካላት የአካል ጉዳተኞች እና አረጋዊያን በፍትሕ ሥርዓት አስተዳደሩ ውስጥ በምስክርነት፣ በተከራካሪነት፣ በመረጃ ሰጭነት ወይም በሌላ መንገድ በእኩልነት ተሣትፎ እንዲያደርጉ የሚያስችላቸውን አመቺ ሁኔታ የመፍጠር ግዴታ አለባቸው፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ጉዳዮችና አቅጣጫዎች

### 7.1 መሻሻል ወይም መለወጥ ስለሚገባቸው ጉዳዮች

ከዚህ ፖሊሲ ጋር የሚቃረኑ ወይም ሊቃረኑ ስለሚችሉ ሕጎችን እና የአሠራር ሥርዓቶችን አስመልክቶ የሚከተሉት አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) ከዚህ ፖሊሲ ጋር የሚቃረኑ ወይም ሊቃረኑ የሚችሉ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ሌሎች ማንኛውም የአሠራር ሥርዓቶች ከፖሊሲው ጋር በሚጣጣም ወይም ፖሊሲውን ለመፈፀምና ለማስፈፀም በሚያስችል መልኩ ሊሻሻሉ ወይም ለውጥ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

(ለ) ፖሊሲው ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ከወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ጋር በተገናኘ የሚከናወን ማንኛውም የሕግ ማሻሻል፣ አዲስ ሕግ የማዘጋጀት ወይም ሌሎች የአሠራር ሥርዓቶች የመዘርጋት ሥራዎች ከዚህ ፖሊሲ በሚቃረን ሁኔታ መሠራት የለባቸውም፤ እንዲሁም ይህንን ፖሊሲ ለመፈፀምና ለማስፈፀም በሚያመች መልኩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com

(ሐ) በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚገኙ የፍትሕ አካላት ይህንን ፖሊሲ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ በሆነ ሁኔታ ለመፈፀምና ለማስፈፀም የሚያስችል የአመራር፣ የአሠራርና የአደረጃጀት ሥርዓቶችን አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡

## 7.2 የፖሊሲው የተፈፃሚነት ጊዜ

ይህ ፖሊሲ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤት